# ያለፈውን እና የአሁኑን ሁኔታዎች በመገምገም
# በኢትዮጵያ ህዝብ አርበኞች ግንባር ተዘጋጅቶ የቀረበ
# የትግል ራእይ

## ግንቦት 30 1998

ይህ ጽሁፍ፣ ለኢህአግ አባላት፣ ደጋፊዎች እና በአጠቃላይ ለሀገራችን ህዝብ ሁሉ ስለ ኢህአግ ራእይ፣ አላማ እና የትግል ስልት መመላከቻ የሚሆን ሰነድ ማስፈለጉን በመረዳት የተዘጋጀ ነው።

ሰነዱ በሶስት አበይት ርእሶች ተከፍሏል። የመጀመሪያው ክፍል የድርጅቱን አመሰራረት ታሪክ በመግቢያነት በማቅረብ፣ ከዚህ ተለምዶ የተገኙትን መሰረታዊ ትምህርቶች በማስተዋወቅ ይደመድማል። ሁለተኛው እና ሶስተኛው የሰነዱ ክፍሎች ደግሞ፣ ለኢህአግ የትግል ራእይ በመሆን እያገለገሉ ያሉትን የብሄራዊ እርቅ መንግስት ምስረታን አስፈላጊነት እና የህገ-መንግስት ጦር መደራጀትን ጠቃሚነት ዘርዘር ባለ መልካቸው ለማቅረብ ይሞክራሉ።

# ማውጫ


የኢትዮጵያ ህዝብ አርበኞች ግንባር አመሰራረት አጭር ታሪክ......................4

ስለ ብሄራዊ የእርቅ መንግስት ምስረታ ጥያቄ ……………………………..8

ስለ ህገ-መንግስታዊ ሰራዊት አደረጃጀት……………………………………12

የትጥቅ ትግሉ የፖለቲካ ክንፍ ስራዎች.........................................................20

ማጠቃለያ…………………………………………………………………23

# የኢትዮጵያ ህዝብ አርበኞች ግንባር አመሰራረት አጭር ታሪክ

ከፋኝ ተብሎ ሲጠራ የነበረው ድርጅት እንደ ኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር በ1974 ዓ.ም. ተጀመረ። የተጀመረበት ልዩ ቦታም ወልቃይት ውስጥ የሚገኘው አቀወርቅ የተባለው ስፍራ ነበር። የጀመሩትም ከደርግና ከወያኔ ጋር የተጣሉ አንዲት ሴትና ሁለት ወንዶች ነበሩ። እነዚህን ሶስት ሰዎች በመከተል ለዚህ ድርጅት ብዙ ሰዎች ህይወታቸውን ሰውተው አልፈዋል።

ከፋኝ ከወያኔ ጋር ፍልሚያ የጀመረው ገና ደርግ በስልጣን ላይ ከነበረበት ወቅት ጀበሮ ነው። በደርግ ዘመን፤ ወያኔን በሰሜን ጎንደር፤ በወልቃይት፤ በአርማጭሆ፤ በጠገዴ እና በጠለምት በመዋጋት ታላቅ ተጋድሎ አድርጎአል። ወያኔም በእነዚህ አካባቢዎች ውስጥ በገጠመው ከፍተኛ ተቃውሞ ምክንያት ጎንደርን መያዝ ስላልቻለም፤ ጎጃምና ጎንደርን ለመቆጣጠር በደብረታቦርና በደጀን በኩል በመዞር ወደ ባህር ዳር መግባት ነበረበት። ከዚያ በኋላ ነበር፤ ለወር ያህል ጎንደር ውስጥ ሲዋጋ የነበረው ቁጥሩ በግምት አንድ ሺ የሚደርስ የደርግ ሠራዊት በትክል ድንጋይ በኩል አድርጎ ወደ አርማጭሆ በርሀ የገባው።

በ1984 እንደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር ይህንን ድርጅት ማጠናከር ያስፈልጋል የሚል ቆራጥ አቋም የወሰድን ወገኖች፤ ከፋኝ ብለን የኢትዮጵያ ህዝባዊ አርበኞች ንቅናቄ በማለት ሰይመን ትግላችንን ለመቀጠል ወሰንን። በዚያኑም አመት በጎረቤት አገሮችና በባህር ማዶ እንዲታወቅ ለማድረግ ታላቅ ጥረት አደረግን።

በ1985 እንደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር ደግሞ፤ የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ያደረጉትን ተቃውሞ ለማፈን ሲል ወያኔ በፈፀመው በደል ምክንያት ብዙዎች ትምህርታቸውን ትተው ከእኛ ጋር ተቀላቀሉን። እነዚህ ወጣቶችም፤ ከዚያን ወቅት ጀምሮ በአመራርና በውትድርና መስኮች በመሰማራት ለንቅናቄው ከፍተኛ አስተዋጽኦ እያበረከቱ ይገኛሉ።

ትግሉ እያደገ ሲመጣም ብዙዎች ከአየር ኃይል፤ ከባህር ኃይል፤ ከአየር ወለድ፤ ከምድር ጦር፤ ከፖሊስ ሠራዊትና ከጠቅላላ የህብረተሰቡ ክፍሎች እንዲሁም ከራሱ ከወያኔ የሸሹ አካላት ከእኛ ጋር በመቀላቀል ለድርጅታችን እድገት አስተዋጽኦ አበርክተዋል።

ድርጅታችን በእንደዚህ አይነት መንገድ ቀስ በቀስ እየተጠናከረ ሳለ፤ በ1987 ኢ.ም ከፍተኛ ችግር አጋጠመን። እርሱም፤ ወያኔ ከ1985 እስከ 1986 (እ.ኢ.አ) ድረስ ከኦነግ ጋር ያደረገውን ከፍተኛ ውጊያ ጨርሶ፤ ፊቱን ወደ ሰሜን በማዞር፤ በጎንደር ክፍለ ሀገር ላይ ሶስት ክፍለ ጦር አዝምቶ፤ ከፋኝን ለማጥፋት ከአደረገው ጥረት በመከተል የደረሰብን ከፍተኛ ጉዳት ነበር።

በዚህ ጥቃት ምክንያት ያጣነውን መልሶ ለማቋቋም፤ በ1987 (እ.ኢ.አ) ወደ ሱዳን በመግባት፤ ጠቅላላ ጉባኤያችንን ሚያዚያ 22 ላይ አድርገን፤ ድርጅታችንን እንደ ቀድሞው በማጠናከር፤ በአገርና በውጭ ሀገራት ውስጥ የነበሩትን መስመሮች እንደገና ዘረጋን።

በ1988 (እ.ኢ.አ) ወያኔ ከሱዳን መንግስት ጋር በፈጠረው አለመግባባት ምክንያት፤ የሱዳኑ መንግስት በከፈተልን ቀዳዳ በመጠቀም በተለያዩ የሱዳን ከተሞች ውስጥ ጽ/ቤቶችን ለመክፈት ቻልን፡፡ ከዚህም በመቀጠል፤ ሠራዊታቱ ተጠናክሮ ወደ አርማጭሆና ወልቃይት ጠገዴ በመሰማራት፤ ከፋኝ የኢትዮጵያ ህዝባዊ አርበኞች ንቅናቄ ከፍተኛ ተጋድሎን ሊያካሂድ ችሏል፡፡

በ1990 (እ.ኢ.አ) በወያኔ እና ሻእብያ መካከል ታላቅ ግጭት ሲፈጠር፤ ሱዳንና ወያኔ እንደ ገና ወደ እርቅ መጡ፡፡ ይህንን እርቅ ተከትሎም፤ ሱዳኖች  የከፈቱትን በር በሙሉ በመዝጋት፤ የአመራር አካላቱን አባላት ይዞ በማሰር እና በፍጥነት አገር ለቅቀው እንዲወጡ በማስገደድ አንገላቷቸው፡፡

ግማሹ ወደ አውስትራሊያ፤ ሌላው ወደ ኒውዜላንድ ሲገባ፤ የተረፍነው ደግሞ እራሳችንን በማጠናከር ከወያኔ ጥቃት ለመዳንና ሰራዊቱንም በበለጠ ለማጠናከር ስንል፤ በ1991 (እ.ኢ.አ) መስከረም 28 ቀን ለኤርትራ መንግስት ፅ/ቤት ለመክፈት እንዲፈቅድልን አመለከትን፡፡ ባመለከትነው መሠረትም ተፈቀደልን፡፡
ጥቅምት 12 1991 (እ.ኢ.አ) በኤርትራ ውስጥ ፅ/ቤታችንን ከከፈትን በኋላም፤ በአርማጭሆ አካባቢ የነበረውን ጦራችንን እንደገና በከፍተኛ ደረጃ እንዲጠናከር አደረግን፡፡

ከፋኝ የኢትዮጵያ ህዝባዊ አርበኞች ንቅናቄ፤ ከዚያም ሌላ በአገር ውስጥ ሲንቀሳቀሱ ከቆዩ ድርጅቶች መሀል አንዱ ከነበረው፤ የኢትዮጵያ ህዝቦች ዲሞክራሲያዊ ግንባር ጋር የአላማ ተመሳሳይነት ስለነበረው፤መጋቢት 22 1991 (እ.ኢ.አ) በተጠራ ስብሰባ ላይ በኢትዮጵያ አንድነት ጥያቄ ላይ በመተማመን፤ በጋራ ከተወያየን በኋላ አዲስ ስም በመሰየም የኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ ኃይሎች አንድነት ግንባርን ፈጠርን፡፡

ከፋኝ የኢትዮጵያ ህዝባዊ አርበኞች ንቅናቄ በገውለል፤ በቃብቲያ፤ በአርማጭሆ ከፍተኛ ጥቃት ሲያደርስ፤ የኢትዮጵያ ህዝቦች ዲሞክራሲያዊ ግንባር ደግሞ አዲገሹን ከተማ ተቆጣጥሮ በወልቃይትም ታላቅ ጥቃት አድርሷል፡፡

በሰኔ 12 1991 (እ.ኢ.አ) የሁለቱን ሀይሎች ሰራዊት አዋህደንም፤ የጋራ የኮማንዶ ትምህርት እንዲሰጥ አድርገናል፡፡ ከዚያ በኋላ ደግሞ፤ በነሀሴ 1991 ኮ/ር መስከረም አታላይ እና አቶ ዮሴፍ ወደ አሜሪካ በመጓዝ ታላቅ የቅስቀሳ ስራ አከናውነው ወደ ሰራዊቱ እንዲመለሱ ሁኗል፡፡ ከዚሁ በመቀጠልም፤ በ1992 (እ.ኢ.አ) መልሶ የማጥቃት ዘመቻዎች ተደርገዋል፡፡ ከእነዚህ ዘመቻዎች መሀልም፤ የኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ ኃይሎች አንድነት ግንባር በወልቃይት ክንፍ በሶላ በቃብቲያ አካባቢዎች ያደረገው የማጥቃት እርምጃ ለምሳሌነት የሚጠቀስ ነው፡፡

በአርማጭሆ አካባቢ የነበረው ክንፍ ደግሞ በአብደራፊእ በአብርሀጅራ ሽመላ ጋር በግጨው አካባቢዎች ታላላቅ የማጥቃት ዘመቻዎችን አድርጓል፡፡ የኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ ኃይሎች እነዚህን መሰል ዓበይት ተግባሮች ለሁለት ተከታታይ ዓመታት ሲፈፅም ቆይቶም፤ በድምሩ አራት የሆኑ ድርጅቶች በህብረት ለመታገል የተዘጋጁ ሁነው ሲገኙም፤ በጥቅምት 7 ቀን 1993 ዓ.ም. ሌላ ህብረት ተፈጠረ፡፡

ይህንን አዲስ ህብረት የፈጠሩት አራት ድርጅቶች የሚከተሉት ነበሩ፡፡

1. የኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ ኃይሎች አንድነት ግንባር - በኮማንደር መስከረም አታላይ የሚመራ

2. የኢትዮጵያ አንድነት አርበኞች ግንባር - በአቶ ተዋት ፓል የሚመራ
3. የኢትዮጵያ አንድነት አርበኞች ዲሞክራሲያዊ ንቅናቄ - በአቶ ተስፋዬ ጌታቸው የሚመራ
4. የቤንሻንጉል ነፃነት ንቅናቄ - በአቶ ጁማን እሩፋኤል የሚመራ

ሆኖም፤ ይህ ህብረት ብዙ ሳይቆይ አንዳንድ መሰረታዊ ችግሮች ገጠሙት። ህብረቱ እንደተመሰረተ አንዳንድ ተንኮልና በውስጡም አፍራሽ ሁኔታዎች መከሰታቸውን ያስተዋለው የኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ ኃይሎች አንድነት ግንባርም ተቃውሞውን አሰማ። ህብረቱ ለሶስት ወር ጊዜ እንኳን ሳይቆይ፤ የድርጅቶቹን መሪዎች በማሰር እና ሰራዊቱን እርስ በእርስ በማጋጨት ሰራዊቱን ለመበታተን ተሞክሮ ነበር።

ነገር ግን፤ ህብረቱ ያመጣውን ችግር ለማስወገድ ሰራዊቱ ቆራጥ አቋም ስለነበረው፤ ስህተቶቹን ለአስራ አምስት ቀናት በቆየ ውይይት አማካይነት በመገምገም ለማረም ተችሏል። ከዚህ ግምገማ በመቀጠልም፤ አንዳንድ ለችግሩ ምክንያት የነበሩትን የአመራር አባላትን በማስወገድ በአራት ተከፍሎ የነበረውን አመለካከት አንድ ወጥ በማድረግ፤ በጥቅምት 1993 ዓ.ም. የኢትዮጵያ ህዝብ አርበኞች ግንባር ተመሰረተ።

ከላይ ከቀረበው የኢህአግ አጭር ታሪክ መመልከት እንደሚቻለው፤ ድርጅቱ አሁን እሚገኝበት ደረጃ ላይ ለመድረስ ብዙ አስቸጋሪ ውጣ ውረዶችን አልፏል። በዚህ ሂደት ውስጥም ብዙ ትምህርቶችን ቀስሟል። ከእነዚህ ትምህርቶች ውስጥ ደግሞ የሚከተሉት ሶስቱ የአሁኑን የድርጅቱን ራእይ ለመቅረጽ ታላቅ አስተዋጽኦ ነበራቸው።

1) ሀገራችንን ገጥሟት የሚገኘው የኤኮኖሚ፤ ፖለቲካዊ፤ ማህበራዊ፤ ሀገራዊ ደህንነት እና የተፈጥሮ አካባቢያዊ ብልሽት ችግሮች ውስብስብነት እና ትልቅነትን መረዳት፤
2) ተመሳሳይ ራእይ ያላቸው ስብስቦች እና አካላት በአንድነት ስር ልዩነቶችን አቻችለው፤ አቅማቸውን አስተባብረው እና አቀናጅተው ለትልቁ የጋራ አላማቸው በመደጋገፍ መንቀሳቀስ እንደሚገባቸው መረዳት፤
3) በተለያዩት የሀገሪቱ ኑሮ ዘርፎች ውስጥ የተከሰቱትን ውስብስብ ችግሮች ለመፍታት መነሻው እና መጀመሪያው ሊሆን የሚገባው ለፖለቲካው ችግር የማያዳግም መፍትሄን መስጠት መሆኑን መረዳት ነበሩ።

የኢህአግ ራእይ ባጭሩ፤ ለእነዚህ ሶስት ግንዛቤዎች የሚሰጥ የተግባር ትልም ነው፤ ማለት ይቻላል። ኢህአግ፤ ሀገራችን የምትገኝበትን አስቸጋሪ ሁኔታ ለመወጣት ኢትዮጵያ ያላትን አቅም ሁሉ አስተባብራ መነሳት እንደሚኖርባት ስለሚያምን፤ ሁሉን ፖለቲካዊ እንቅስቃሴ ያካተተ፤ በመርህ ላይ የተመሰረተ የእርቅ መንግስት መመስረትን ጉዳይ ቅድሚያ ይሰጠዋል።

ነገር ግን፤ ይህንን ታላቅ ሀገራዊ ራእይ ለማሳካት ብዙ ችግሮች እንዳሉም፤ ኢህአግ አይስተውም። በተለይ፤ ዋናው እንቅፋት የወያኔ አምባገነናዊ አገዛዝ እና ፈሊጥ መሆኑን ያምናል። በመሆኑም፤ ኢህአግ ይህንን ችግር የሚወጣበት መንገድ ከላይ የተጠቀሰውን ሀገራዊ ራእይ እንዳያረክሰው ይጠነቀቃል። በዚህ አቅጣጫ በማሰብም የትግል ትልሙ ዋናውን ሀገራዊ ራእይ እንዲያጎለብት አድርጎ ቀርጾታል። እንደ እውነቱ ከሆነ፤ የኢህአግ የትግል ትልም በዚህ አይነት መንገድ በመቀረጹም፤ የትግል ትልሙ የራእዩ አካልም ነው፤ ማለት ይቻላል።

ይህ የኢህአግ የትግል ትልም ሶስት ዋነኛ ገጽታዎች አሉት፡፡ እነርሱም፡--

1) የወያኔ እብሪት ተሰብሮ፤ እንደ አንድ ድርጅት ብቻ ሁኖ በእርቅ በሚመሰረተው መንግስት ድርድር ውስጥ እንዲሳተፍ ማስገደድ የሚቻለው፤ የወያኔን የመሳሪያ አቅም በህዝባዊ ወታደራዊ እንቅስቃሴ በማዳከም ብቻ ስለሆነ፤ የመሳሪያ ትግሉን ማፋፋም፤
2) በእርቅ ላይ የተመሰረተ መንግስት መቋቋምን አስፈላጊነት ከሚያምኑ ማናቸውም ፖለቲካዊም ሆነ ወታደራዊ እንቅስቃሴዎች ጋር በህብረት መንቀሳቀስ፤
3) ለወያኔ እብሪት መሰረት የሆነው የጠብመንጃ ሀይል፤ በእርቅ በተመሰረተው መንግስት ወቅት ተመልሶ እንዳይመጣ ለማድረግ ሲባል፤ ተቋማዊ መጠብቅ ከአሁኑ ማዘጋጀት ስለሚገባ፤ የኢህአግን ጦር የህገ-መንግስት አስከባሪ ጦር ጥንስስ አድርጎ ማደራጀት፤ እና ሌሎች ወታደራዊ እንቅስቃሴዎችም ይህንን ራእይ ተቀብለው ህገ-መንግስታዊ ጦር እንዲሆኑ መጣር፤ ናቸው፡፡

በዚህ ሰነድ ውስጥ እኒህ ጉዳዮች በሁለት አበይት ርእሶች ተከፍለው፤ ዘርዘር ባለ መልክ ይቀርባሉ፡፡ የመጀመሪያው አቢይ ርእስ ኢህአግ ስለእርቅ መንግስት ምስረታ አስፈላጊነት ያለውን ራእይ ሲያቀርብ፤ ሁለተኛው ደግሞ በህገመንግስታዊ ጦር አደረጃጀት ላይ ያተኩራል፡፡

## ስለ ብሄራዊ የእርቅ መንግስት ምስረታ ጥያቄ

እርቅ በበደል ምክንያት የተፈጠረ ጥላቻ እና የስሜት ቁስል የወደፊቱን ተስፋ እንዳያጨልሙት የሚረዳ ማህበረሰባዊ መላ ነው። የእርቅ አካሄድ እና አፈጻጸም እንደ እየበደሉ አይነት፣ እንደ እየማህበረሰቡ ባህላዊ ባህርያት፣ እንደ እየታሪካዊ ወቅቱ እና እንደየተደራዳሪዎቹ አቅም እና ተፈጥሮ የተለያዩ መንገዶችን ሊከተል ይችላል።

በዘመናችን በተለያዩ ሁኔታዎች የተከናወኑ ፖለቲካዊ እና ማህበረ-ሰባዊ እርቆች ብዙ ናቸው። ለምሳሌነት ያህልም፣ በሀገራችን ከጣሊያን ወረራ መልስ፣ በደቡብ አፍሪካ ከአፓርታይድ ስርአት ማብቃት ጋር የተከተለውን እና በቅርቡ ደግሞ በጎረቤታችን በሱዳን የተካሄደውን ለአብነት ያህል በአጭር በአጭሩ ጠቅሰን እናልፋለን።

እንደሚታወቀው ሁሉ፣ በተለያዩ ምክንያቶች በጣሊያን ወረራ ወቅት ለፋሺስት ኢጣሊያ በማደር ወገናቸውን ሲወጉ የነበሩ ብዙ ባንዳዎች ነበሩ። ጣሊያን ከተባረረ በኋላ አጼ ኃይለ ስላሴ ተመልሰው ስልጣን ሲይዙ ከወሰዷቸው የመጀመሪያ እርምጃዎች መሀል፣ ለባንዳዎች አጠቃላይ ምህረት መስጠትን ነበር።

በርግጥ፣ ይህ የአጼ ኃይለስላሴ እርምጃ የመነጨው ከግል የፖለቲካ ስልጣን ስሌት እንጂ ከይቅር-ባይነት አልነበረም፣ የሚሉ ወገኖች አሉ። እኛም ይህንን ጥርጣሬ እስከተወሰነ ደረጃ ድረስ ለመቀበል ብንዘጋጅ እንኳን፣ ንጉሰ ነገስቱ ይህንን ምህረት በሰጡበት ወቅት ከወረራው በተከተሉ ምክንያቶች ነባሩ ስርአት በከፍተኛ ደረጃ ተናግቶ የነበር ብቻ ሳይሆን፣ የእንግሊዝ ጊዜያዊ አስተዳደርም በሀገሪቱ ላይ ተጭኖ የነበረበትን ሁኔታ አላገናዘቡም፣ ማለት ግን አይቻለንም።

በዚያን ወቅት፣ ብልህ የፖለቲካ ሰው  በተቻለ መጠን ሀገር በቀል የሆኑ አካላትን ሁሉ ማሰባሰብ እንጂ ማከፋፈል አይገባው እንደነበር እንረዳለን። ንጉሰ ነገስቱ ለባንዳዎች የሰጡት አጠቃላይ ምህረትም፣ የፖለቲካ መሰረታቸውን ለመጠበቅ የጠቀማቸው እንደነበር እንቀበላለን። ነገር ግን፣ ይህ ተግባር ሀገሪቱ በተለያዩ ሰርጦች ሳትከፋፈል እንድትቀጥል ለማድረግ አስተዋጽኦ ያበረከተ የፖለቲካ ተግባር እንደነበርም፣ መካድ አይቻልም።

ሁለተኛው ምሳሌ ደግሞ፣ በ1991 (እ.ኤ.አ) በደቡብ አፍሪካ ከአፓርታይድ ስርአት ማክተም ጋር ተያይዞ ወደመጣው ስርአት ይወስደናል። እንደሚታወቀው ሁሉ፣ በደቡብ አፍሪካ የፖለቲካ የበላይነትን ይዞ የኖረው የጥቂቶቹ ነጮች ዘረኛ አገዛዝ በብዙኃኑ የደቡብ አፍሪካ ነዋሪ ላይ ብዙ በደሎችን ለዘመናት ሲፈጽም የኖረ ነበር። የዚህ አገዛዝ በደል ጥልቀት ህዝቡን በቀለም ብቻ ሳይሆን፣ በጥቁሩ ህዝብ መሀልም በዘውግ ላይ የተመሰረቱ ብዙ መለያየቶችን ያስከተለም ነበር። በ1990 (እ.ኤ.አ) ይህ አገዛዝ በህዝባዊ ትግል መሸነፉ አይቀሬ እየሆነ ሲሄድ፣ አንዱ አስፈሪ ጉዳይ ሀገሪቱ ወደ እርስ-በርስ ጦርነት የመግባቷ ከፍተኛ ምናልባታዊነት ነበር። የኔልሰን ማንዴላ እና አብረዋቸው የነበሩት አንጋፋ የአፍሪካ ናሽናል ኮንግሬስ መሪዎች ታላቅነት በተቀዳሚነት የተመሰከረውም፣ ይህንን አስቸጋሪ ሁኔታ ለመወጣት ሲሉ በወሰዱት አቅጣጫ ነው።

ይህ አቅጣጫም፣ በደቡብ አፍሪካ የብሄራዊ እርቅ መንግስትን መመስረት ነበር፡፡ የእርቁ መንፈስ ደግሞ ላለፉ በደሎች ፍትሀዊ እልባትን በመስጠት የሚቋጭ ሳይሆን፣ ያለፈውን ሁሉ ወደመርሳት የተገፋ በመሆኑ፣ ይህ ምርጫ ለኔልሰን ማንዴላ ምን ያህል ከባድ እንደነበር መገመት አያዳግትም፡፡ ክብደቱ የሚመነጨው ማንዴላ በአፓርታይዱ ስርአት ለ27 አመታት በመታሰራቸው አይደለም፡፡ ከዚህ ይልቅ፣ ለተበዳዩ ጥቁር ህዝብ ለዘመናት አሰቃቂ በሆነ መንገድ ሲበድልህ ከኖረው በዳይህ ጋር ያለፈውን ሁሉ ትተህ እና እረስተህ፣ ተቻችለህ መኖር አለብህ ብሎ መናገሩ ላይ ነበር፡፡

በአንጻሩ ደግሞ፣ በደቡብ አፍሪካ የእርቅ መንግስት ካልተመሰረተ በሀገሪቱ ውስጥ ሊከተል ይችል የነበረው እልቂት ግልጽ ሁኖ የሚታይ ነበር፡፡ ይህንን ሁኔታ ተጋፍቶ ለመሄድ ቢሞከር እንኳን፣ ምእራባውያኑ መንግስታት በተሸናፊው የነጮች መንግስት ዙሪያ ለነበረው ህዝብ የነበራቸው መድሎኛ ድጋፍ በግልጽ የሚታይ ነበር፡፡ በዚህም ምክንያት፣ የሽግግር መንግስቱን በሁለት እግሩ ለማቆም በጣም አስቸጋሪ ሁኔታ ይፈጠር እንደነበር መካድ አይቻልም፡፡ በዚህም መሀከል፣ የሀገሪቱን መዋእለ ንዋይ ተቆጣጥረው ይገኙ የነበሩት በአፓርታይዱ መንግስት ዙሪያ የነበሩት ጥቂቶቹ ነጮች ስለነበሩ፣ በእነርሱ ዘንድ አመኔታ የሌለው መንግስት ቢመሰረት፣ የደቡብ አፍሪካ የኤኮኖሚ ልማት ጉዳይ ለረጂም ጊዜያት የሚታሰብ ሊሆን አይችልም ነበር፡፡

የአፍሪካ ናሽናል ኮንግሬስ በእንዲህ አይነቱ አጣብቂኝ ውስጥ በወደቀበት ሰአት ነበር፣ የመሪዎቹን ታላቅነት፣ ልበ-ሰፊነት እና አርቆ አስተዋይነት ያስመሰከረው "ዘ ትሩዝ ኮሚሽን" በመባል የሚታወቀው ተቋም ኃሳብ የፈለቀው፡፡ በአቡነ ዴዝሞንድ ቱቱ ሰብሳቢነት የሚመራው ይህ ኮሚሽን፣ ስራው፣ በአፓርታይድ ወቅት ተፈጸሙ ስለተባሉት በደሎች ምስክሮችን በመጥራት እውነቱን እና ሀቁን ማረጋገጥ ነበር፡፡ በዚህ ሂደት ውስጥ በዳዮች በምስክርነት እየተጠሩ በመጠየቅ፣ ስለፈጸሟቸው በደሎች ዝርዝር እውነቶች ሊረጋገጡ ቢችሉም፣ ተበዳዮች ለበደላቸው አቻ የሆነ ፍትህ እንዳላገኙ እሙን ነው፡፡ የዚያ ዘመን በደሎች ዝርዝር እውነት በአደባባይ ሲጋለጥ፣ በአፓርታይድ ምክንያት በህብረተሰቡ ውስጥ ሰርጾ የኖረውን በሽታ በማከም ለወደፊቱ ትውልድ የተሻለ ተስፋ ሊገኝ ይችላል፣ የሚለው እምነት ብቻ ነበር መጽናኛው፡፡

የመጨረሻው ምሳሌ ደግሞ ለሀገራችን ሁኔታ እና ጂኦግራፊ ቅርበት ወዳለው፣ በቅርቡ በሱዳን ውስጥ ወደተካሄደው እርቅ ይመልሰናል፡፡ በቅርቡ፣ የተለያዩ አለም አቀፍ አካላት እና የውጭ መንግስታት በሱዳን መንግስት ላይ ባሳደሩት ጫና ምክንያት፣ ከሰላሳ ለበለጡ አመታት በደቡቡ እና በሰሜኑ የሱዳን ክፍሎች መሀከል ሲካሄድ የኖረውን የርስበርስ ጦርነት በእርቅ መንገድ ለመፍታት የሚያስችል ስምምነት ተፈጥሯል፡፡ የእርቁም ዋነኛ ጭብጦች በሁለቱ ወገኖች መሀከል የፖለቲካ ስልጣን ክፍፍልን መፍጠር፣ ሁለቱ ወገኖች የሱዳንን ተፈጥሮ ሀብት የሚጋሩበትን ስርአት ማደራጀት እና ከተወሰኑ አመታት በኋላ ደግሞ የደቡቡን ሱዳን ህዝብ የወደፊት ፍላጎት ማወቅ የሚያስችል ህዝበ-ውሳኔን ማካሄድ ናቸው፡፡

የሱዳኑ እርቅ ለግጭቱ መንስኤ የሆኑትን ጉዳዮች መርምሮ፣ ለችግሩ የማያዳግም መፍትሄ ለመስጠት የሞከረ አይደለም፡፡ በመሆኑም፣ ይህ እርቅ ከተበዳዩ ወገን በኩል ሙሉ ይቅር ባይነት፣ ከበዳዩ ወገን ደግሞ ለተፈጸመው በደል ፀፀትን የሚጠይቅም አልነበረም፡፡ ሁለቱን ወገኖች ወደ ድርድር እንዲገቡ ያስገደዳቸው ሁኔታ፣

በአየበኩላቸው የፈለጉትን ነገር ለመፈጸም አለመቻላቸው ብቻ ነበር። በመሆኑም፤ የእርቁ ይዘት ሽግግራዊ ሰላምን ለማምጣት ያለመ ብቻ ነው። (ይህ ማለት ግን፤ ጊዜ መሀሪ ነውና!--የተጀመረው እርቅ ወደ ሙሉ እርቅ አያመራም ማለት አይደለም።)

ወደ ሀገራችን ሁኔታ ስንመለስ፤ የበደሉ ዋነኛ ምንጭ የኢህአዴግ አምባገነናዊ ስርአት ነው። የዚህ በደል ቀጥተኛ መገለጫ፤ ኢህአዴግ እና የወያኔ መንግስት በህዝብ፤ ለወያኔ ባልገበሩ የተለያዩ ማህበረ ሰባዊ ተቋማት እና በተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች ላይ የሚፈጽሙት አይን ያወጣ እና ቅጥ ያጣ ግፍ ነው። ይህ በደል የሚገፋው ደግሞ፤ ህዝብን ከህዝብ፤ እስላሙን ከክርስቲያኑ፤ ኦሮሞውን ከአማራው፤ ትግሬውን ከጉራጌው፤ ሌላው ሳይቀር አድዋውን ከአጋሜው ወዘተ... ለማጋጨት ተብሎ በተነደፈው የወያኔ ‹‹ፖለቲካ›› ሽፋን ነው።

በርግጥ፤ በኢትዮጵያ ህዝብ ጨዋነት እና አርቆ አስተዋይነት ምክንያት ይህ እኩይ ተግባር ወያኔ አሰበው ደረጃ ላይ ገና አልደረሰም። ሆኖም፤ ይህ ቁስቆሳ ለዘመናት በሰላም ጎን ለጎን አብረው በኖሩ ህዝቦች መሀል ያስፈጸማቸውን በደሎች መካድም አይቻልም። ከዚህ በላይ የሚያስፈራው ደግሞ፤ ህዝቡ ለነጻነቱ ለመታገል ያለውን ቁርጠኛነት ባሳየ መጠን፤ የወያኔ መንግስት የምትቀረው መንጠልጠያ ይህች አይነትዋ ዘረኛነት ብቻ በመሆኗ፤ ወያኔ ሀገራችንን ወደ ርስ-በርስ ጦርነት ለመክተት ተግቶ የሚሰራ መሆኑ ነው። በሀገራችን ሊከተል የሚገባው ብሄራዊ እርቅ ዋነኛ አላማም፤ ይህንን አደጋ በማስወገድ የወያኔን ተንኮል ማክሸፍ ነው።

ከዚህ አላማ አንጻር፤ በህዝቦች መሀል የስሜት መሻከሮች እንዳይደነድኑ የሚያስችሉ አንዳንድ ተግባራትን ከወዲሁ ማከናወን ቢቻልም፤ ይህ ብሄራዊ እርቅ በአስተማማኝ መሰረት ላይ ሊቆም የሚችለው የብሄራዊ እርቅ መንግስት ከተመሰረተ በኋላ ብቻ ነው። ይህ መንግስት ሊመሰረት የሚችለው ደግሞ፤ ወያኔ የእርቅ መንግስት ምስረታን አስፈላጊነት እንዲያምን ሲደረግ፤ ወይም የሚተማመንበት የመሳሪያ ሀይል ተንዶ እንደድርጅት ብትንትኑ ሲወጣ ብቻ ነው። ማናቸውም ቢሆኑ ግን፤ያለ መሳሪያ ትግል ተጽእኖ ሊመጡ የሚችሉ አይደሉም።

በርግጥ፤ ኢህአዴግ በፈቃዱ በእርቅ መንግስት ለመሳተፍ ቢመርጥ፤ የኢህአግ ተወዳጁ ምርጫ ነው። ኢህአግ ለዚህኛው አማራጭ የሚያደላበት ምክንያት የጦርነትን ሰቆቃ በተቻለ መጠን ለማስወገድ ካለው እምነት ብቻ የሚመነጭ ሳይሆን፤ ማናቸውም የፖለቲካ እንቅስቃሴዎች የተሳተፉበት የእርቅ መንግስት ምስረታ፤ የሀገራችንን መሰረታዊ ችግሮች ለመፍታት የመጀመሪያው ርምጃ መሆን ይኖርበታል ከሚለው ራእዩ የሚከተልም ነው።

ኢህአግ ለእርቅ መንግስት ምስረታ ያለው ታማኝነት የመጠንከሩን ያህል ደግሞ፤ ይህ እርቅ በጽኑ የመርህ መሰረቶች ላይ መቆም እንደሚገባው ያምናል። እኒህም የመርህ መሰረቶች፤ ፍትሀዊነት፤ ዘለቄታዊነት  እና ጥፋቶች እንዳይደገሙ የሚያስችሉ መተማመኛዎችን መጨበጥ ናቸው። በኢ.ህ.አ.ግ እምነት፤ በእንደዚህ አይነት መርህ ላይ የተመሰረተ እርቅ በኢትዮጵያ ውስጥ በአሁኑ ወቅት ሊካሄድ የሚችለው፤ እርቁ የሚከተሉትን አራት ተግባራት ሲያካትት ብቻ ነው።

1) በደልን የፈጸሙ አካላት ላጠፉት ጥፋት ተመጣጣኝ ቅጣትን ሲያገኙ፤
2) ተበዳዮች ለተፈጸመባቸው በደል ተመጣጣኝ ካሳ ሲቀበሉ፤

3) ለበደሎች መንስኤ የሆኑ ጉዳዮች ተመርምረው በማያዳግም መንገድ ሲታረሙ እና ተቋማዊ መጠብቆች ሲደረጉላቸው፤
4) እነዚህን ከላይ የተዘረዘሩትን ሶስት ጉዳዮች ለማስፈጸም የሚችል፤ በግልጽ እና በገሀድ የሚሰራ፤ ስለገለልተኛነቱ እና ነጻነቱ በህዝብ ዘንድ የሚታመንበት አካል ሲቋቋም።

ኢ.ህ.አ.ግ፤ ይህንን መሰል ፍትሀዊ የእርቅ አጀንዳ ተግባራዊ ማድረግ፤ ብዙ ትግል የሚጠይቅ ጉዳይ መሆኑን ያምናል። ለዚህ ተግባራዊነት ዋናው መሰናክልም፤ ወያኔ የዚህን አጀንዳ አስፈላጊነት በውዴታ የማይቀበል መሆኑ ነው። ስለዚህ፤ የብሄራዊ እርቅ አጀንዳ ለኢ.ህ.አ.ግ ራእይ ብቻ ሳይሆን፤ የትግል መስመርም ነው።

በኢህአግ እምነት፤ ወያኔ ፈለገውም አልፈለገውም፤ ተሳተፈበትም አልተሳተፈበትም፤ ዛሬም ይሁን ነገ፤ የወያኔ ስርአት ሲወድቅ በኢትዮጵያ ውስጥ መምጣት የሚገባው መንግስት ከላይ የተዘረዘሩትን አራት ጉዳዮች በብቃት የሚተገብር የብሄራዊ እርቅ መንግስት ነው። ኢህአግ ይህንን ውጤት ለማስከተል ዋነኛ አድርጎ የሚወስደው የትግል ስልቱም፤ የወያኔን መንግስት በመሳሪያ ትግል ማድቀቅን ነው።

ኢ.ህ.አ.ግ መሳሪያን እንደዋነኛ የትግል ዘዴው አድርጎ ይውሰድ እንጂ፤ ይህ ትግል በሌሎች ተግባራት መታገዝ እንደሚገባውም ያምናል። እኒህ ተግባራት እንደእየሁኔታው እና የትግሉ እድገት ደረጃ መልካቸውን ሊለዋውጡ የሚችሉም ናቸው። ነገር ግን፤ በማንኛውም መልካቸው ቢቀርቡም፤ ከላይ የተቀመጡትን አራት መርሆአዊ የእርቅ መንግስት ተግባራት ለማቅረብ የሚረዱ መሆን እንደሚገባቸው ኢ.ህ.አ.ግ በጽናት ያምናል።

ለማጠቃለል ያህል፤ የኢ.ህ.አ.ግ ትግል ግብ፤ በኢትዮጵያ ከሌሎች ተመሳሳይ አላማ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር፤ ፍትሃዊ እና ዴሞክራሲያዊ ስርአትን መመስረት ነው። ይህንን ትግል ለሀገሩ በጎ የሚያስብ ወገን ሁሉ ሲደግፈው፤ ጸረ-ሀገር ሀይላት ደግሞ አጥብቀው እንደሚዋጉት አይጠረጠርም። ይህ ትግል፤ እውነተኛ የህግ የበላይነት በሀገሪቱ ውስጥ እንዲነግስ የሚዋጋ በመሆኑ፤ ወያኔ በቅጥረኞቹ አማካይነት ለራሱ መገልገያ አድርጎ የሚመነዝረውን እና የሚተረጉመውን ወያኔያዊ “ህግ” በማያወላዳ መንገድ ያጋልጣል። በዚህም፤ ወያኔ የመንግስት ስልጣንን ተቆጣጥሮ ለመቀጠል የሚያስችል የሞራል ቁመና እንደሌለው ያረጋግጣል። የብሄራዊ እርቅ አጀንዳም ይህንን የፍትህ እና ዴሞክራሲያዊ ስርአት መስፈን ትግል ለማሳካት የሚጠቅም ትልቅ ስትራቴጂ ነው። ሌላው ቢቀር፤ ወያኔን ሳያካትት እንኳን፤ በሀገሪቱ ውስጥ ለሚገኙ ማናቸውም ቡድኖች እና ስብስቦች ሁሉ በፍትህ ላይ የተመሰረተ የእርቅ እና የፖለቲካ መደራደሪያ መድረክ በማቅረብ፤ የሰላም እና የፍትህ ሀይሎች ተባብረው እንዲንቀሳቀሱ ለማድረግ የሚያስችል ነው።

ስለዚህም፤ ኢ.ህ.አ.ግ ማንኛውም ሀገር ወዳድ ሁሉ፤ በግልም ሆነ በቡድን ደረጃ በዚህ አጀንዳ ዙሪያ አቅሙን አስተባብሮ እንዲንቀሳቀስ ጥሪውን ያቀርባል።

# የህገ-መንግስታዊ ስራዊት መደራጀት አስፈላጊነት

በግንቦት 97ቱ ምርጫ እንደታየው፣ ህዝብ ለለውጥ ዝግጁ ነው:: የግንቦቱ ምርጫ፣ ህዝቡ በጋራ ጭንቀት የተሳሰረ፣ በስልጣን ላይ ባለው መንግስት ላይ ከፍተኛ ተቃውሞ በሆዱ ይዞ እንደሚኖር ግልጽ አድርጓል።

የኢትዮጵያ ህዝብ በምርጫው ወቅት በገዥው ፓርቲ እና በተቃዋሚዎች መሀል በተደረጉት ክርክሮች ውስጥ ተነስተው በነበሩት ጉዳዮች ላይ የነበሩትን ልዩነቶች ለመረዳት ባሳየው የግንዛቤ ብቃት እና ባሳየው ስነስርአት፤ ሰላማዊ እና ህጋዊ በሆነ ስልጡን የፖለቲካ ሂደት ውስጥ በብቃት መሳተፍ እንደሚችል ታይቷል ። ህዝቡ፤ የተወሳሰቡ የድምጽ ምርጫ ወረቀቶችን በመጠቀም የምርጫ ካርዱን በሚገባ ጥቅም ላይ በማዋልም የሚፈልገውን እንደሚያውቅ አረጋግጧል::

በምርጫ 97 ሂደት ውስጥ የታየው የህዝብ ድምጽ መሰረቅ እና የምርጫው መጭበርበር ሁኔታ፤ ኢትዮጵያን ዴሞክራሲያዊ ለማድረግ የሚደረገው ጥረት መሰረታዊ ችግሮች የት ላይ እንደሆኑ በግልጽ አሳይቷል። የሃገራችን የዴሞክራሲያዊ ፖለቲካ ሂደት ድክመቶች ከህዝብ የፖለቲካ ብስለት ማነስ፣ የአመራረጥ ታክቲክን ከአለማወቅ፣ ከምርጫ ታዛቢዎች እጥረት፤ አግባብነት ያለው ምርጫ ለማኪያሄድ ከሚያስፈልግ የሰለጠነ የሰው ሃይል እና ድርጅት እጥረት እንዳልሆነ ታውቋል:: ህዝቡ ለዴሞክራሲያዊ መብቶቹ መከበር በጽናት ለመታገል ካለመፈለጉ እንዳልሆነም ታይቷል::

ዋነኛው ችግር፤ በስልጣን ላይ ያለው የወያኔ አምባገነናዊ መንግስት ለሰላማዊ እና ለዴሞክራሲያዊ የፖለቲካ ሂደት መሳካት የፖለቲካ እምነት የሌለው ከመሆኑ የሚከተል መሆኑ ተረጋግጧል:: የወያኔን የሰላማዊ ፖለቲካ ፍላጎት ማጣት፣ ሽፍጥና የፖለቲካ ህገወጥነት መቋቋም የሚችሉ እና ወያኔን ሌላው ቢቀር የራሱን ህገመንግስት እንዲያከብር የሚያስገድዱ ነጻ ተቋማት አለመኖራቸውም ገሃድ ሆኗል:: እኒህን መሰል ተቋማት አለመኖራቸው እና አለመደርጀታቸው ደግሞ፤ በኢትዮጵያ ወሳኝ የሆነውን የሰላማዊ የፖለቲካ ህይወት እና የሰላማዊ የስልጣን ሽግግር እንዳይሳካ የሚያደርገው፣ ሃገሪቱንም ደግሞ ደጋግሞ ከፍተኛ ውድመት እና መዘዝ ወደ አለው የአመጽ አዙሪት ውስጥ የሚደፍቃት ዋነኛ ምክንያት መሆኑ ተረጋግጧል:::

ኢህአግ፤ የኢትዮጵያ ህዝብ በግንቦት 97ቱ ምርጫ ወቅት የሰጠው ድምጽ መጭበርበሩ፤ ለህዝቡም ሆነ ለፖለቲካ ድርጅቶች ታሪካዊ እና ሃገራዊ የሆነ ትምህርት አስተምሮ አልፏል የሚል እምነት አለው:: ተቃዋሚዎቹም ሆኑ ህዝቡ ድምጹን ለማስከበር የወሰዳቸው እርምጃዎች፤ ከወያኔ ተጽእና ነጻ የሆነ የምርጫ ቦርድ ባለመኖሩ፣ በምርጫ ቦርድ አማካይነት ቅሬታው መፍትሄ እንዳላገኘ አይቷል:: በምርጫ ቦርድ ያልተቻለውን በፍርድ ቤቶች በኩል ለማስፈጸም የተደረገው ሙከራም ቢሆን፣ ፍርድ ቤቶቹ በወያኔ ፈቃድ ብቻ የሚሰሩ በመሆናቸው፤ ፍትሀዊ እልባት እንዳላገኘ ተረጋግጧል:: ከእዚህ አልፎ፤ ህዝብ በህገ-መንግስቱ የተቀመጠለትን የሰላማዊ ተቃውሞ መብት በመጠቀም በሰላማዊ ሰልፍ እና በስራ ማቆም አድማዎች ድምጹን ለማስከበር ያደረገው ህጋዊ እና ህገመንግስታዊ እርምጃም፤ ወያኔ እንዳሻው በሚያዝዘው የጦር፤ የፖሊስ እና የደህንነት ሃይል አማካይነት ወደሞት፣ እስራት እና ስደት ተቀይሮ አብቅቷል::

ባጭሩ፤ የግንቦት 97ቱ ምርጫ በአንድ በኩል፤ በሃገራችን መሰረታዊ ለውጦች እንዲደረጉ የሚሻ ከፍተኛ የህዝብ ፍላጎት እና መነሳሳት መኖሩን ሲያረጋግጥ፤ በሌላ በኩል ደግሞ፤ ኢህአግ አስቀድሞ እንደገመተው፤ ይህ መነሳሳት ሰላማዊ እና ህጋዊ በሆነ መንገድ ሊሳካ አለመቻሉን አሳይቷል። ሆኖም፤ ኢህአግ፤ ይህ ሂደት በዚህ ንኡስ ርእስ ስር የተዘረዘሩትን፤ የህዝብ መነሳሳትን፤ የልሁቁ እና የህዝቡን መልካም ግንኙነት፤ የወያኔን ፖለቲካ ርቃኑን ማስቀረት ወዘተ... የመሳሰሉትን ታላላቅ ድሎች አስመዝግቦ ያለፈ መሆኑን ደግሞ ይገነዘባል። ከዚያም አልፎ፤ የኢትዮጵያን ህዝብ ፍላጎት ከግቡ ለማድረስ፤ በሰላማዊ መንገድ የተገኙትን ድሎች ቆንጥጦ መገኘት እና ማዳበር እንደሚጠቅምም ያምናል። ይህ ሁሉ ተብሎም ግን፤ ሰላማዊ ትግሉ ሊጓዝ እሚችልበት ድረስ ተጉዞ እንደቆመ በመመልከት፤ ከአሁን በኋላ በሀገራችን ሰፍኖ የሚገኘውን የአምባገነንነት ስርአት ለመዋጋት ከትጥቅ ትግል የተለየ ዋነኛ የትግል ስልት ሊኖር እንደማይችል በጽኑ ይገነዘባል።

የወያኔ መንግስት ለሃገራችን እና ለህዝቦቿ ደንታ የሌለው፤ ጸረ ሰላም እና ጸረ ዴሞክራሲያዊ ዘረኛ እና አምባገነናዊ የጥቂት በስልጣን እና ከስልጣን በሚመጣ ተጠቃሚነት የሰከሩ ኋላ ቀር ሃይሎች ስብስብ መሆኑን፤ ኢህአግ ቀደም ብሎ ያውቃል። በመሆኑም፤ 1) የወያኔን መሰረታዊ ባህርይ በሚገባ በመረዳት፣ 2) ወያኔ በሃገራችን ወሳኝ በሆኑት መንግስታዊ ተቋማት ላይ እንደልቡ የሚያዝዝባቸው መሆናቸውን በማጤን፤ 3) በእኒህ መሰል ቁልፍ ተቋማት ውስጥ በከፍተኛ የሃላፊነት ስፍራዎች ላይ የተሰገሰጉት (ከማል በድሪን የመሳሰሉ!) የራሳቸው ሰብአዊ ክብር የሌላቸው አካላት መሆናቸውን በመገምገም፤ እነዚህ ኋላቀር ሁኔታዎች በተወሰነ ደረጃ በተወገዱባቸው ሃገሮች የተካሄዱ የሰላማዊ ለውጥ ትግሎችን የመሰሉ አካሄዶች በሃገራችን ሊካሄዱ ይችላሉ የሚል እምነት ግንባራችን የለውም።

የሃገራችን የፖለቲካ ለውጥ ጥያቄ የሃገራችንን ተጨባጭ ሁኔታ ያገናዘበ እና የተረዳ ምላሽን የሚጠይቅ ነው። ኢትዮጵያ ጆርጂያ ወይም ዩክሬን አይደለችም። በእነዚህ እና በሌሎች ተመሳሳይ ሃገሮች ውስጥ የሚገኙ የመንግስት፣ የሲቪል እና የሚሊተሪ የአስተዳደር ባለስልጣናት የእውቀት እና የባህል እድገት ደረጃ በሃገራችን ከሚገኙት (ከማል በድሪን፤ ወርቅነህ ገበየሁን እና ሳሞራ ዩኑስን ከመሳሰሉት) ክብር-የለሽ ሆዳሞች ጋር ሲነጻጸር የሰማይ እና የምድርን ያህል የተራራቀ ነው። ስለዚህ፤ በእነዚህ ሀገሮች ውስጥ የተካሄዱ የሰላማዊ ትግል ስልቶችን እንዳለ መኮረጅ ለሀገራችን ይጠቅማል ብለን አናምንም። እንዲያውም፤ እንዲህ አይነቱ ኩረጃ ከእዚህ ቀደም በሃገራችን ከውጭ ተኮርጀው ህዝባችንን እና ሃገራችንን ለችግር እንደዳረጉት የርእዮተ-አለም ኩረጃዎች ሁሉ፤ ችግራችንን ሊያባብሰው ይችላል የሚል ስጋት አለን።

ግንባሩ በሰላማዊ መንገድ ሊደረግ የሚችል ትግል አብቅቶለታል ባይ ነው። ሆኖም፤ ይህ የትግል ስልት አሁንም ይቻላል የሚል እምነት ያላቸው ወገኖች ካሉ፤ ለእምነታቸው ተገቢውን አክብሮት በመስጠት፤ ኢህአግ ለእነዚህ አካላት የሃገራችንን የተለየ ሁኔታ ግምት ውስጥ ያስገባ በበቂ ጥናት ላይ የተመሰረተ ማሻሻያ እንዲያደርጉበት ሊያሳስብ ይወድዳል።

በኢህአግ እይታ፤ የግንቦት 97 ምርጫ ሂደት በማያወላዳ መንገድ ያረጋገጠው ጉዳይ፤ ዴሞክራሲ ለወያኔ የህዝብን የፖለቲካ አመለካከት መሰለያ ፈጣን እና ርካሽ መሳሪያ መሆኑን ነው። ወያኔን ተቃውመው የተሰለፉ በተቃውሟቸውም ጸንተው የቆሙ የህዝብ ወገኖች ሁሉ የት እንደደረሱ እናውቃለን። መሪዎቹን አስሮ በእውነተኛዎቹ ተቃዋሚ ድርጅቶች ምትክ እና በስማቸው ሌሎች ተለጣፊ ተቃዋሚዎች

ተፈልፍለዋል፡፡ ስለዚህ፤ ሰላማዊ ትግልን ለመግፋት የሚያስቡ ወገኖች፤ የወያኔን ህጋዊነት እና የወያኔን ቃል አምኖ የተደረገው እንቅስቀሴ ያስከተለውን መዘዝ በሚገባ ማጤን ይኖርባቸዋል፤ እንላለን፡፡

ኢህአግ፤ ሰላማዊ ትግል ብቻውን ወያኔን ከአምባገነናዊ እብሪቱ ፈቀቅ ያደርገዋል፤ የሚል እምነት የለውም፡፡ ወያኔ ያለበትን የህዝብ ተቃውሞ እና የህዝብን አልገዛም ባይነት በመረዳት፤ ህዝብ እና ተቃዋሚ ፓርቲዎች የሚያቀርቧቸውን የሰላማዊ እና ህጋዊ የፖለቲካ ስርአት ዋስትናዎች ለመመስረት ፈቃደኛ የሚሆን አይደለም፡፡ ወያኔ በከፍተኛ ወታደራዊ ጉልበቱ የሚተማመን በመሆኑ፤ ማንኛውንም ሰላማዊ እንቅስቃሴ እያፈነ ለመኖር ያሰላ ነው፡፡ ህዝብ ከፍተኛ የለውጥ ፍላጎት ቢኖረውም፣ ማለቂያ የሌላቸውን የወያኔ የእመቃ እርምጃዎች በመቋቋም ትግሉን እየተቀጠቀጠም ቢሆን መቀጠል የሚችለው፤ የመከራው ማለቂያ ተስፋን ሊመለከት ሲችል ብቻ ነው፡፡ አለበለዚያ፤ ተስፋ መቁረጥ፣ የአርበኛነት እና የሃገር ፍቅር ስሜት መውደም፣ ግላዊ የሆነ ኢሞራላዊ እና በሙስና የሚመራ የግለሰቦች ህይወት መስፋፋት፣ ስደት እና ውርደት ይጠናከራሉ፡፡ ለኢትዮጵያ መዳከም እና ህዝቦቿ እንደህዝብ የሚያሳዩት የነጻነት እና የክብር ስሜት ለሚያበሽቃቸው ለእነመለስ ዜናዊ እና ለሀገራችን መሰረታዊ የውጭ ጠላቶች የተመቻቸ ሁኔታ ይፈጠራል፡፡

ስለዚህም፤ የሰላማዊ ትግል እምነት ከልኩ አልፎ ወደ ቀኖናነት መለወጥ አይኖርበትም፤ እንላለን፡፡ የሀገራችንን አስከፊ የሆነ ሁኔታ ለመለወጥ ሲባል የሚቀረጹት የትግል ስልቶች በሙሉ የህዝቡን ደህንነት እና ተስፋ ግምት ውስጥ ያስገቡ እና ህዝቡን ለወያኔ እመቃ የማያጋልጡ መሆን ይኖርባቸዋል፤ ብለንም እናምናለን፡፡

ኢህአግ በሀገራችን ለዘመናት ከስልጣን ውጣ ውረድ ጋር የተቆራኙ የአመጽ እንቅስቃሴዎች ያስከተሏቸውን መዘዞች ያውቃል፡፡ ይህንን ሃቅ መሰረት አድርጎ ግን፤ አመጽ ሁልግዜም መከራ አራቢ እንጂ ከመከራ መውጫ መሳሪያ አይሆንም፤ ከሚል ርእዮተአለማዊ ቀኖና ጋር አይጣበቅም፡፡ በቁጥርም ቢሆን፤ በአለማችን አስቸጋሪ ሁኔታዎችን በአመጽ በመወጣት ዘለቄታዊነት ያለውን ዴሞክራሲያዊ ስርአት የገነቡት ሃገሮች፤ ሰላማዊ በሆነ መንገድ ከመጡት ሃገሮች እንደሚበልጡ ይረዳል፡፡ ኢህአግ ሰላማዊ ትግል የሚሰራው ለሰላማዊ ትግል የተመቻቹ ሁኔታዎች ሲገኙ እንጂ፤ እነርሱ በሌሉበት ቦታ ባርነትን የመቀበያ ቀመር ሊሆን ይችላል፤ ብሎ ይሰጋል፡፡ ከዚህም በላይ፤ ለሀገራችን ህልውና አስጊ የሚሆኑ ሁኔታዎችን ሊያመቻች እንደሚችልም ይረዳል፡፡ "የህንድ አስተዳዳሪ በእንግሊዝ የቅኝ ግዘት ቫይስሮይ ምትክ የናዚ ጀርመኒ ጄነራል ቢሆን ኖሮ፤ የጋንዲ እንቅስቃሴ እና የህንድ ህዝብ እጣ ምን ይመስል ነበር? ብሎ መጠየቅ ተገቢ ነው፡፡

ኢህአግ፤ አመጽ ዛሬ ህዝባችን የደረሰበትን የፖለቲካ ብስለት ግምት ውስጥ በማስገባት ከተቀረጸ እና ከተደራጀ ወደ ተመኘነው የዴሞክራሲ እና የሰላም መንደር ለምናደርገው ጉዞ ዋነኛ የትግል ስልት ይሆናል፤ የሚል እምነት አለው፡፡ ይህንን ማድረግ የሚቻለው ግን፤ ከተቀየረው የሃገራችን ሁኔታ እና ከተደረሰበት የፖለቲካ እድገት ጋር የሚመጥን፤ ይህንን እድገት ወደፊት ወሳጅ እንጂ ወደኋላ ቀልባሽ ያልሆነ ራእይ ሲኖረን ብቻ ነው፡፡ ከእዚህም በመነሳት፤ የኢትዮጵያ ህዝብ አርበኞች ግንባር በኢትዮጵያ የተቀየረውን ሁኔታ ግምት ውስጥ ያስገባ የአመጽ ትግል ራእይ ምን መሆን አለበት የሚል ጥያቄ በማንሳት ምላሹን ሰጥቷል፡፡

## የትጥቅ ትግሉ ራእይ እና መርሆዎች

የሃገራችንን ሁኔታ በአጠቃላይ እና የወያኔን መሰረታዊ ባህርይ በተለይ ላጤነ፤ የትጥቅ ማንሳት ጥያቄ ብዙም ኢያከራክርም። ለኢህአግ ዋነኞቹ ጥያቄዎች የትጥቅ ትግሉ አስፈላጊነት ላይ ሳይሆን፤ ትግሉ ምን ለማምጣት ነው? በምን ራእይ እና አላማ ላይ ነው የሚቆመው ? መከራ አምራች ከሆኑት ያለፉ የአመጽ ትግሎች እንዴት ይለያል? የመለየቱስ ዋስትና ምንድን ነው? ሌላ አምባገነን ድርጅት፤ ሌላ አምባገነን መሪ እንደማይፈጠር ዋስትናው ምንድን ነው? እንደገና ወደ ሌላ የአመጽ አዙሪት ሃገራችንን የማይወስድበት መተማመኛውስ ምንድን ነው? የሚሉት ናቸው።

የሃገራችን የፖለቲካ ችግር ዘለቄታዊ መፍትሄ የሚያገኘው ሰላም እና የህግ የበላይነት የሰፈነበት ስርአት በሀገራችን ውስጥ ሲመሰረት ብቻ መሆኑ አያጠራጥርም። ችግሩ የሚመጣው፤ ወያኔ እንዲህ አይነቱ የፖለቲካ ህይወት እንዳይኖር በማድረጉ ነው። ሁላችንም የምንመኘውን ከሃገሪቱ የፖለቲካ ህይወት አመጽን የማስወገድ ምኞታችንን እያጨናገፈ ያለው፤ በስልጣን ላይ የሚገኘው የወያኔ አገዛዝ ነው። አመጽን ከፖለቲካው መድረክ ካላጠፋን፤ ሰላም እና መረጋጋት እንደማይኖሩ እሙን ነው። ቀጣይነት ያለው የኢኮኖሚ እና የፖለቲካ ስርአት ግንባታም አይቻልም። ማህበራዊ ችግሮቻችንንም አንፈታም።

በፖለቲካው መስክ ደግሞ የአመጽ መንስኤ የፖለቲካ ልዩነቶች መኖር ጉዳይ ሳይሆን፤ እነዚህን ልዩነቶች ሰላማዊ እና ስልጡን በሆነ መንገድ ማስተናገድ የሚቻልበት ሁኔታ መፈጠር አለመቻሉ ነው። ለዚህ ደግሞ ዋነኛው ምክንያት፤ በሙስና የበከተው የወያኔ አምባገነናዊ አገዛዝ ነው።

በግንቦት 97ቱ ምርጫ ወቅት፤ የፖለቲካ ፓርቲዎች ሰፊ ቅስቀሳ እና ክርክር ሲያደርጉ፤ ህዝብ በጥሞና አዳመጠ እንጂ ሁካታ አልፈጠረም። ሁካታው የመጣው ባለጠመንጃው፣ ጠመንጃ የሌለውን ህዝብ ድምጽ ልዝረፍ ብሎ ሲነሳ ነበር። የሃገራችን ህዝብ፣ የፖለቲካ ልዩነቶች ሰላማዊ መፍትሄ ተነፍገቻቸው ወደ ግጭት ሲያመሩ በሃገር እና በህዝብ ላይ የሚያደርሱትን ከባድ ጉዳት ያለፈ ታሪኩን በማስታወስ የተመለከተ እና ያስተዋለ ነው። በመሆኑም፤ በግንቦት 97 ላይ በተካሄደው ምርጫ ላይ ከፍተኛ ተስፋ አሳድሮ ነበር።

ነገር ግን፤ ያ ሂደት ከግቡ ሳይደርስ በወያኔ እመቃ ታፍኖ ተቀልብሷል። ይህንን ቅልበሳ ያሳኩትም፤ የወያኔ አገልጋዮች ሁነው የተቀረጹት የሀገሪቱ መስተዳድራዊ ተቋማት ናቸው። የኢህአግ የትጥቅ ትግል ዋነኛ አላማም፤ ኢትዮጵያን ዴሞክራሲያዊ የማድረግ ሂደት ድክመቶች ሆነው የተገኙትን እና ህዝብም ሆነ ሁሉም የተቃዋሚ ፓርቲዎች የተስማሙባቸውን፣ ለሰላማዊ እና ህጋዊ የፖለቲካ ትግል ከለላ የሚሆኑትን፤ በሁሉም ህዝብ እና በሁሉም የተቃዋሚ ፓርቲዎች ዘንድ የሚደገፉ፤ ህገ-መንግስታዊ የነጻ መስተዳድራዊ ተቋማት ግንባታን እውን ማድረግ ነው።

የአንድ ሀገር ነጻ ተቋማት ዋስትና መኖር ሊረጋገጥ የሚችለው፤ ህገ-መንግስታዊ የጦር፣ የፖሊስ እና የስለላ ሃይል ተቋማት በአንድ ሃገር ውስጥ ሲኖሩ ብቻ ነው። እነዚህ ሃይሎች ለአንድ ፓርቲ አገልጋይ ሁነው መደራጀታቸው ግን፤ የሌሎችን ነጻ ተቋማት ምስረታ የማይፈቅድን ሁኔታ የሚያስከትል ብቻ ሳይሆን፤ ቢፈቀድም የይስሙላ እንጂ እውን እና ቀጣይነት ያለው ህልውና እንዳይኖራቸው የሚያደርግን ሁኔታ ይፈጥራል። በአንጻሩ ደግሞ፤ የጦር ሃይሉ ህገ-መንግስታዊ እና ከፓርቲዎች ተጽእኖ ነጻ እና ገለልተኛ ሆኖ በሚቆምበት ሃገር ውስጥ፤ በፖለቲካ ፓርቲዎች

ስምምነትም ሆነ በፓርላማ አማካይነት የሌሎች ነጻ ተቋማት ምስረታ አስቸጋሪ አይሆንም።

ትጥቅ ትግል ውስጥ ለተሰማሩ ወገኖቻችን በአንክሮ ማሳሰብ የምንወደው ጉዳይም፤ ይህንን የመሰረታዊ ለውጥ ቅድመ-ዝግጅት እንዲመክሩበት ነው። በተለምዶ ሲካሄድ የኖረው አይነት፤ አንድን ፓርቲ ወደ ስልጣን የሚያወጣ የትጥቅ ትግል በብዙው የሀገራችን ህዝብ ዘንድ ተቀባይነት የሚኖረው አይመስለንም። ኢህአግ እንዲህ አይነቱን ሙከራ ለማድረግ የሚሹ አካላት በሙሉ፤ ውለው አድረው ከህዝብ እና ከሌሎች የፖለቲካ ድርጅቶች ጋር የሚያጋጯቸው ሁኔታ ሲፈጠር፤ የመሳሪያ አቅማቸውን ወደመጠቀም በመዞር፤ ለአምባገነናዊ ስርአት መመስረት ጥርጊያ ሊከፍቱ ይችላሉ፤ የሚል ስጋት አለው። አንድ ፓርቲ በራሱ ስልጣን ከያዘ በኋላ በግሉ በሚያዛቸው የጦር እና ሌሎች ሃይሎች አማካይነት የነጻ ዴሞክራሲያዊ ተቋማት ምስረታን አከናውናለሁ ቢልም፤ የተለያዩ የፖለቲካ ድርጅቶች እና ሌሎችም ትጥቅ ያነሱ ቡድኖች ባሉበት ሃገር ውስጥ እንዲህ አይነቱ አካሄድ አዝሏቸው የሚንዛቸው አደጋዎች ብዙ ናቸው።

በኢህአግ አመለካከት፤ ከዚህ ሁሉ የተሻለው አማራጭ መንገድ፤ ዛሬ ጉዞው የተደናቀፈውን የሃገራችንን ሰላማዊ እና ህጋዊ የፖለቲካ ሂደት ለማቃናት የሚያስችል፤ ከሁሉም የፖለቲካ ፓርቲዎች ነጻ የሆነ እና በሁሉም የፖለቲካ ፓርቲዎች የሚደገፍ ነጻ የጦር ሃይልን ማቆም ብቻ ነው።

ኢህአግ፤ ዛሬ የሃገራችን ህዝብ የደረሰበትን የፖለቲካ ብስለት እና የተቃዋሚ ፓርቲዎች ከጠየቋቸው የነጻ ተቋማት ምስረታ መሃል ዋንኛ የሆነውን፤ ለሰላም እና ለዴሞክራሲ መስፈን አስፈላጊ የሆነውን ነጻ የህገ መንግስታዊ ሰራዊት ምስረታ ለማገዝ ቁልፍ ሚና መጫወት እንዳለበት ያምናል። ኢህአግ የትጥቅ ትግል ጀምሮ በመንቀሳቀስ ላይ እና በወያኔም እመቃ የተነሳ የትጥቅ ትግል ይደረግ እያለ በመጮህ ላይ የሚገኘውን ህዝብ ድጋፍ እየሳበ የሚገኘውም፤ የራሱን የፓርቲ ፖለቲካ ገጽታ እና የስልጣን ምኞት በማስወገድ፤ ከሁሉም የፖለቲካ ፓርቲዎች ነጻ የሆነ፣ አላማው በህዝብ ዴሚክራሲያዊ ተሳትፎ ተቀባይነትን ላገኘ ህገመንግስት ተገዥ የሆነ የጦር ሃይል መገንባት እርሾ ሁኖ ለማገልገል በመቆሙ ነው።

በሃገራችን እስከ ዛሬ ድረስ የተቋቋሙት ትጥቅ ያነሱ ሃይሎች ሁሉ፤ በበላይነት የሚያሿቸውን የፖለቲካ ፓርቲዎች ወይም ግንባሮች የፖለቲካ እምነቶች እና አላማዎች ለማስፈጸም የቆሙ ናቸው። በተለያዩ የፖለቲካ ድርጅቶች መሃል የሚደረግ ሰላማዊ የፖለቲካ ትግል በማይፈቀድበት ሃገር ውስጥ፤ የፓርቲዎች ወደ ስልጣን መውጫ ብቸኛው መንገድ የአመጻ ሃይልን በማደራጀት ሁኖ ኑሯል። ስልጣን በአመጽ ከተያዘ በኋላም፤ በአመጽ ከስልጣን ከመወገድ በስተቀር ስልጣንን ከተቃዋሚዎች ጋር በመጋራት ለሃገር እና ለወገን እርባና ያለው ስራ በመስራት ለመንቀሳቀስ ፍላጎቱ ኑሮም አያውቅም።

በርግጥ፤ የመንግስትም ይሁን የተቃዋሚ ሃይሎች ወታደራዊ ክንፍ የፖለቲካ ፓርቲዎችን ፖሊሲዎች አስፈጻሚ ቁልፍ አካል ተደርጎ በሚታይበት ወይም ሲታይ በተኖረበት ሃገር ውስጥ፤ ከፖለቲከ ድርጅቶች ነጻ ስለሚሆን ህገ-መንግስታዊ የጦር ሃይል ማውራት አዲስ ነገር ነው። ከተለመደው የፖለቲካ ድርጅቶች ርእዮተ አለም እምነት እና ህዝብም በተመክሮው ከሚያውቀው የፖለቲካ ድርጅቶች ባህል በመነሳት፤ ይህ የትግል አቅጣጫ እንግዳ ነገር ሁኖ ቢታይም፤ አይገርምም።

ኢህአግ፤ የሃገራችንን ችግር በጥልቀት በመመርመር፤ ይህንን የቆየ የአመላካከት እስር ቤት ሰብሮ ቁልፍ የሆነ የፖለቲካ ችግራችንን የሚወጣበትን ይህንን መፍትሄ አግኝቷል፡፡ በመሆኑም፣ ኢህአግ፤ በትጥቅ ትግል ላይ የተሰማሩ ሌሎች አካላትም ሆኑ የፖለቲካ ድርጅቶች፤ ‹‹ከእዚህ በፊት ያልተለመደ አካሄድ ነው›› ከሚለው አሉታዊ አመለካከት ራሳቸውን ነጻ አድርገው፤ "የእንደዚህ አይነቱ የጦር ሃይል መደራጀት፤ ዛሬ በሃገራችን አስፈላጊ እና ቁልፍ የችግሮቻችን መፍትሄ ነው ወይስ አይደለም?" እሚለው ላይ እንዲያተኩሩ ያሳስባል፡፡

በኢትዮጵያ ህዝብ አርበኞች ግንባር እምነት፤ በህዝብ እና ዴሞክራሲያዊ በሆኑ የፖለቲካ ድርጅቶች አይነ፤ የእንዲህ አይነቱ ሰራዊት መኖር አስፈላጊነት የሚያጠያይቅ አይሆንም፡፡ ይልቁንም፤ ጥያቄው "እንዴት ሊፈጠር ይችላል?" የሚል ብቻ ነው፡፡ በኢህአግ ግምገማ መሰረት አራት መንገዶች ቢኖሩም፤ ከእነዚህ መሃከል ግን እውኑ አማራጭ አንዱ ብቻ ሁኖ ይታያል፡፡ ለማነጻጸር ይረዳ ዘንድ ግን፤ እነዚህ አራት መንገዶች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

**1-በወያኔ እጅ ያለውን የሃገሪቱን ጦር ህገ-መንግስታዊ ማድረግ፡፡**

የመጀመሪያው መንገድ፤ የጦር ሃይሉን ሁሉም የሃገሪቱ የፖለቲካ ድርጅቶች በጋራ መክረው፤ በስምምነት በሚያቋቁሙት ኮሚሽን አማካይነት አሁን ካለበት የወያኔ ተገዥነት ነጻ ማውጣት ነው፡፡ ይህ ሊሆን ቢችል ኑሮ፤ ሃገሪቱም ሆነች ህዝቦቿ ከብዙ መከራ በቀላሉ በወጡ ነበር፡፡ እንደ እውነቱ ከሆነ፤ ወያኔ ከእለት ሆዱ አሻግሮ ዘለቄታዊ ጥቅሙን ለማየት የሚያስችል አይን ቢኖረው ኑሮ፤ ለራሱም ቢሆን ይህ ጥሩ አማራጭ ነበር፡፡ ነገር ግን፤ እንዲህ አይነቱ አማራጭ ወያኔን ስልጣን የሚያሳጣ በመሆኑ፤ ወያኔ ተገድዶ ካልሆነ በስተቀር በውዴታ የሚስማማበት እንዳልሆነ ግልጽ ነው፡፡ ወያኔን ጠንካራ የትጥቅ ተቃውሞ ቢገጥመው ግን፤ መሪዎቹ እንኳን ባይስማሙ፤ የጦርነትን ገፈት የሚቀምሱት የጦር መኮንኖችና እና ተራ ወታደሮች የቀረበላቸውን ፍታህዊ አማራጭ ለመቀበል የሚገደዱበት እድል ሰፊ ይሆናል፡፡ ከዚህም በመከተል፤ ሁሉም የፖለቲካ ድርጅቶች በተስማሙበት መሰረት በተቋቋመ ከሚሽን አማካይነት፤ አሁን ወያኔ የሚያዝበት ሠራዊት እራሱን ወደ ህገ መንግስታዊ ሰራዊትነት ሊቀይር ያችላል፡፡ ይህ መሆን ቢችል፣ ህገ- መንግስታዊ ሰራዊት ለመመሰረት ሲባል የሚቀሰቀሰው ግጭት ከሚያስከትለው የህይወት እና የንብረት ጥፋት ሃገርን እና ወገንን ማትረፍ ይቻላል፡፡ አሁን ከሚታየው ሁኔታ መገምገም እንደሚቻለው ግን፤ እዚህ ደረጃ ላይ ለመድረስ ገና ብዙ ትግል ያስፈልጋል፡፡

**2--በሌሎች የፖለቲካ ድርጅቶች የሚመሰረት፡፡**

ሁለተኛው አማራጭ ደግሞ፤ ሌሎች የፖለቲካ ድርጅቶች ለራሳቸው የፖለቲካ መርሃ ግብር ማስፈጸሚያነት ያቋቋሚቸውን ሰራዊቶች፤ ወያኔን በሚያሸንፉበት ወቅት ወደ ህገ-መንግስታዊ ሰራዊትነት የሚለውጡበት ሁኔታ ነው፡፡ ይህ አማራጭ ከላይ በተራ ቁጥር ‹1› ስር ከተጠቀሳው የመጀመሪያው አማራጭ ያልተለዩ ብዙ ውስብስብ አደጋዎችን ያዘለ ነው፡፡ በመጀመሪያ፤ የእንዲህ አይነቱ ሰራዊት ስልጠና እና ትምህርት የአንድን ፓርቲ ህልውና ለማስጠበቅ የተደራጀ በመሆኑ፤ የፖለቲካ ድርጅቱ በቀላሉ ይህንን ህልውናውን የሚያስጠብቅ ሰራዊት በፍላጎቱ እንዲነጠቅ ያለመፍቀዱ አደጋ አለ፡፡ ሰራዊቱም ቢሆን፤ ከአንድ ፓርቲ ሞግዚታዊ ጥበቃ ውጭ ህልውና አይኖረኝም ብሎ ስለሚያስብ፤ በፓርቲው ላይ ከፍተኛ ተጽእኖ በማድረግ፤ ከፖለቲካ ስልጣን የማይርቅበትን ሁኔታ ማስቀጠሉን በፈቃዱ የማይተውበት ምናልባታዊነት ከፍተኛ ነው፡፡ ከወዲሁ ደግሞ፤ ህብረተሰቡ በተለያዩ የፖለቲካ

ድርጅታዊ ድባቦች ተከፋፍሎ በሚገኝበት ሁኔታ ውስጥ፤ አንድ የፖለቲካ ድርጅት ለብቻው ተነጥሎ ወያኔን ለመፈታተን የሚያስችለውን የትጥቅ ትግል በአንድ የፖለቲካ ፓርቲ ፕሮግራም ስር አስተባብሮ መግፋት መቻሉ አጠራጣሪ ነው:: በአንድ አጋጣሚ በቂ አቅም አዳብሮ ቢገኝ እንኳን፤ ግጭቱ ገና ከመጀመሪያው ከወያኔ ጋር ብቻ ሳይሆን፤ ተመሳሳይ የራሳቸው ሰራዊት ካላቸው ሌሎች የፖለቲካ ድርጅቶች ጋርም ሊሆን ይችላል:: እንዲህ ከሆነ ደግሞ፤ ይህ ችግር አቅምን የሚከፋፍል እና የሚያዳክም ብቻ ሳይሆን፤ የህዝብን መከራ የሚያገዝፍ እና ሃገርንም ወደ ከፋ አደጋ ውስጥ የሚጨምርም ይሆናል::[1]

### 3- የተለያዩ የፖለቲካ ድርጅቶች የሚፈጥሩት ግንባር

ይህ መንገድ ከላይ በሁለተኛ አማራጭነት ከተጠቀሰው እጅጉን የተሻለ መንገድ ቢሆንም፤ ድርጅቶቹ ከወያኔ ጋር ያላቸው ትግል ሲያበቃ፤ በመሃከላቸው በሚነሱ የፖለቲካ ልዩነቶች ምክንያት፤ መልሰው ርስ በርሳቸው ጦር ሊማዘዙ የሚችሉበትን አደጋ ግን አያስወግድም:: ግንባር ሁሌም ቢሆን፤ የፖለቲካ ድርጅቶች ዋናውን ጠላታቸውን ለመጋፈጥ አቅም ሲያንሳቸው የሚፈጥሩት ህብረት ነው:: ዋናው ጠላት መዳከም ሲጀምር ግን፤ የግንባሩ አባላት የተጓዳኞቻቸውን አቅም ለመፈታተን የሚፈልጉበት ሁኔታ ሊፈጠር ይችላል:: ማናቸውም የየራሳቸውን የጦር ሃይል ማጣት የማይፈልጉ ከሆኑ ደግሞ፤ ሁሉም በየፊናው ትጥቁን እያጠበቀ ለማይቀረው ግጭት የሚዘጋጅ ይሆናል:: ይህም ሌላ ዙር የርስ በእርስ ግጭት በቀላሉ ሊቀሰቅስ ይችላል::

### 4- የፖለቲካ አላማው እራሱን ህገ-መንግስታዊ የጦር ሃይል ለማድረግ አልሞ የተነሳ የትጥቅ ትግል::

እንዲህ አይነቱ የትጥቅ ትግል ገና ከጅምሩ የሀገሪቱ የዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ መሰረታዊ ችግሮች እንደሆኑ በታመነባቸው ጉዳዮች ላይ ያተኮረ ነው:: የነጻ ተቋማት ግንባታ ችግር፣ በተለይ ደግሞ ከፖለቲካ ድርጅቶች ነጻ የሆነ ህገ-መንግስታዊ ሰራዊት አለመኖር ችግር፣ የሃገራችን የፖለቲካ ችግር ቁልፍ ጥያቄ ነው ብሎ በመነሳቱ፤ የአላማ ጥራት እና ጽናት ይኖረዋል:: የተፈለገውን ህገ-መንግስታዊ ሰራዊትን የማቆምን ግብ ለማሳካት፤ የተሻለ ዝግጅት እና ድርጅት ይኖረዋል:: ህገመንግስታዊ ሰራዊት በመፍጠር ሁሉም የፖለቲካ ድርጅቶች በነጻነት እና በህጋዊነት የሚንቀሳቀሱበት ሃገራዊ የፖለቲካ ቀጠና የመፍጠር ፍላጎት እንጂ፤ የፖለቲካ ድርጅቶችን ተክቶ የመስራት አላማ የሌለው በመሆኑ፤ ህዝባዊ እና ዴሞክራሲያዊ የፖለቲካ ድርጅቶች በጠላትነት የሚያዩት አይሆንም:: በተለይ ይህ አይነቱ እንቅስቃሴ በቅድሚያ ምንም አይነት ወታደራዊ ክንፍ በሌላቸው የፖለቲካ ድርጅቶች እና ወታደራዊ ትግል ከሚያደርጉ ድርጅቶች ጋር በሚደረግ ስምምነት መሰረት ግልጽ አላማ ይዞ የሚንቀሳቀስ ስለሚሆን የአለመተማመን ችግሮቹ አነሰተኛ ይሆናሉ::

እንደተባለው የህገ-መንግስታዊ ሰራዊት ዋናው አላማ ለሁሉም የፖለቲካ ድርጅቶች ሰላማዊ እና ህጋዊ በሆነ መንገድ በነጻ መንቀሳቀስ የሚችሉበትን ሁኔታ ማመቻቸት ነው:: ይህንን አይነቱን አላማ ይዞ የሚጀምር የትጥቅ ትግል ትምህርቱም

---

[1] በነገራችን ላይ፤ ኢህአግ በእዚህ ጉዳይ ላይ እራሱን በመገምገም፤ ቀደም ብሎ የተጠቀሰውን ማስተካከያ ለማድረግ የተገደደበት ዋነኛ ምክንያት ይህንን ችግር በመገንዘቡ ነው:: ሌሎችም የሰራዊት ክንፍ የማቆም አላማ ያላቸው ወይም ያቆሙ የፖለቲካ ድርጅቶች ከላይ የተባለውን በጥሞና በማሰብ ለመፍትሄው በጋራ መስራት አለባቸው የሚለውም በዚሁ ምክንያት ነው::

ስልጠናውም ህገ-መንግስታዊ እና ቁመናውም ከማንም ፓርቲ ጋር ያልወገነ ሰራዊት መሆን ነው። እንዲህ አይነቱ ሰራዊት አሁን ባለንበት ሁኔታ በቀላሉ በብዙ የፖለቲካ ድርጅቶች እና ደጋፊዎቻቸው ሊደገፍ ይችላል ብለን እናምናለን። በሃገራችን ዴሞክራሲያዊ ሁኔታ የለም በማለት የትጥቅ ትግል ከጀመሩ የፖለቲካ ድርጅቶችም ጋር ቢሆን መቀራረብ የሚያስችል መስመር ነው። አላማው ስልጣን የመያዝ ሳይሆን ሰላማዊ የፖለቲካ ትግል ያለምንም ተጽእኖ ማድረግ የሚቻልባቸውን ሁኔታዎች መፍጠር በመሆኑ፤ ማናቸውንም ጉዳዮች ለህዝብ ለማቅረብ እና በህዝብ ለመዳኘት የሚፈልጉ የፖለቲካ ሃይሎች ሁሉ የሚደግፉት ይሆናል።

ይህ እንቅስቃሴ ለሀገር እና ለህዝብ የሚጠቅምን የመደራደርን፣ የመቻቻልን እና የእርቅን መንፈስ የያዘ፣ በየደረጃው የሚገኝ የሰላም እና የእርቅ እድልን ለመጠቀም ፈቃደኛ ሆኖ የተደራጀ ይሆናል። ከወያኔ ባርነት እራሱን ነጻ በማውጣት የህገ-መንግስታዊ ሰራዊት አካል ለመሆን ከሚፈልገው የሰራዊቱ አካል ጋር ለመነጋገር እና አብሮ ለመስራት ዝግጁ ነው። ዞሮ ዞሮ የእዚህ ሰራዊት ተግባር የሃሳብ ልዩነቶች እና የፖለቲካ ልዩነቶች በሰላም መስተናገድ የሚችሉበትን፤ የህዝብ ድምጽ እና ውሳኔ የሚከበርበትን ሁኔታ መፍጠር በመሆኑ፤ ሰራዊቱ የፖለቲካ እምነት እና አመለካከት የበላይ ተቆጣጣሪ፤ ፈቃጅ እና ከልካይ ሊሆን የሚችልበትን እድል ከአነሳሱ የዘጋ ነው። እንዲህ አይነቱ ህገ-መንግስታዊ ሰራዊት በትግሉ ወቅት እራሱን « ህገ መንግስታዊ ሰራዊት » በማለት ቢንቀሳቀስም፤ እውነታኛ ህገ-መንግስታዊ ሰራዊትነቱ የሚረጋገጠው፤ ሁሉም የፖለቲካ ድርጅቶች ዴሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ መክረው እና ህዝብን አሳትፈው በሚያጸደቁት ህገ-መንግስት አማካይነት ይሆናል።

ኢህአግ መንግስታዊ አስተዳደር ባልተቋቋመበት ሁኔታ ውስጥ የህገ-መንግስት አስከባሪ ሃይል ሁኖ መንቀሳቀስ የሚያስከትላቸውን ችግሮች በአግባቡ አጢኗቸዋል። የመንግስት አስተዳደር ባልተመሰረተባቸው እና በጦርነት ሁኔታ ውስጥ ሊተገበሩ የማይችሉ የህገ-መንግስት አንቀጾች አሉ። በእንዲህ አይነት ሁኔታዎች ውስጥ ሊደረጉ የሚገቡ ጉዳዮችን ከወዲሁ ዘርዝሮ ማስቀመጥ ባይቻልም፤ አንዳንድ ቅድመ ዝግጅቶች እና ጥናቶች ሊካሄዱ እንደሚችሉ እና እንደሚገባቸው ግን፤ ኢህአግ ያምናል።

ኢህአግ፤ የህገ-መንግስታዊ ጦር መደራጀት አስፈላጊነት በተለያዩ የፖለቲካ ድርጅቶች ዘንድ ገና ቅቡልነትን ባላገኘበት ሁኔታ ውስጥ፤ ይህንን መስመር ማስተዋወቅ እና ማኽዘብ ትልቅ ስራን እንደሚጠይቅ ይገነዘባል። በዚህ ስራ ውስጥ ከተለያዩ የትጥቅ እና የፖለቲካ እንቅስቃሴዎች ጋር ሊደረጉ የሚገባቸው ውይይቶች፤ መመካከሮች እና ትግሎች ራሳቸውን የቻሉ የፖለቲካ ስራዎች ሁነው የሚወጡም ናቸው። ከእነዚህ በተጨማሪ ደግሞ፤ ስለ ብሄራዊ እርቅ መንግስት ምስረታ በሚያትተው ክፍል ውስጥ የተዘረዘሩት ጉዳዮች ትጉህ የፖለቲካ ስራን ይጠይቃሉ።

ስለዚህም፤ የኢህአግ አላማ ለሀገሪቱ ህገ-መንግስታዊ ጦር እርሾ ሁኖ ማገልገል ቢሆንም፤ በተግባር አስገዳጅነት ምክንያት ይህንን ራእያችንን የሀገራችን ፖለቲካ እንቅስቃሴዎች በአሁኑ ወቅት ከሚገኙበት እውነታ ጋር እንድናስታርቀው ተገድደናል። ከዚህም በመከተል፤ እንቅስቃሴው በአሁኑ ወቅት ከፖለቲካ ስራ ሙሉ ለሙሉ እጁን ታጥቦ ሊወጣ አለመቻሉን መቀበል ግዴታችን ነው።

# የትጥቅ ትግሉ የፖለቲካ ክንፍ ስራዎች

## 3-1 የብሄራዊ እርቅ አጀንዳን በተመለከተ፤

- የተፈጸሙ በደሎችን (በግለሰቦች፤ ቡድኖች፤ ድርጅቶች፤ ተቋማት፤ ህዝቦች) ዝርዝር ብቃት እና ጥራት ባለው ሁኔታ መሰብሰብ እና ማቀናጀት፤
- እነዚህን በደሎች በተቻለው መንገድ ሁሉ፤ ለአለም አቀፉም ሆነ ለሀገራችን ህዝቦች ሁሉ ማስተዋወቅ፤
- የኢ.ህ.አ.ግ የቅርብ ጊዜ ፖለቲካዊ ግብ፤ ወያኔ ሊሰብክ እንደሚሞክረው ጸረ-ሀገራዊነት ሳይሆን፤ ለሀገር ዘለቄታዊ መረጋጋትን የሚያረጋግጥ የእርቅ መንግስት ምስረታ መሆኑን የሚያስተዋውቅ ዘመቻ መክፈት፤
- ኢ.ህ.አ.ግ የእርቅ መንግስት የሚመሰረት ከሆነ አመጽን የማይገፋ ሰላምን ወዳድ መሆኑን የሚያስተዋውቅ ዲፐሎማሲያዊ ዘመቻ መክፈት፤
- የብሄራዊ እርቅን አስፈላጊነት በኢህአዴግ አባላትም አካባቢ ሆነ ለእነርሱ ድጋፍን በሚሰጧቸው የህዝብ አካላት አካባቢዎች ተቀባይነትን እንዲያገኝ የፖለቲካ እና የፕሮፓጋንዳ ስራዎችን መስራት፤
- በሀገራችን የተዘረጋውን የበደል ስርአት ለመዋጋት ሲሉ ወደ አመጽ በተሰማሩ ሌሎች አካላት አካባቢ ሁሉ፤ ይህ አጀንዳ ተቀባይነትን እንዲያገኝ መጣር፤
- በአመጽ ላይ የተሰማሩ ወታደራዊ እንቅስቃሴዎች ተግባር፤ ከእለት አንድ ጀምሮ፤ ነጻ ባወጧቸው አካባቢዎች ውስጥ ሁሉ፤ ተጨባጭ ሁኔታው እስከፈቀደ ድረስ፤ የህግ የበላይነትን ማስከበር እንዲሆን መጣር፤ (በምንም አይነት፤ እነዚህ ተግባራት ከድል በኂላ በሚመሰረተው ስርአት ውስጥ ይከናወናሉ፤ በሚል ተስፋ ተዘናግቶ አለመቀመጥ!)
- ለበደል መንስኤ የሆኑትን ጉዳዮች እና መፍትሄአቸውን ማጥናት። ለመፍትሄነት ስምምነት ላይ የተደረሰባቸውን ጉዳዮችም መተግበር።[2]

**3-2-1-** ህገ-መንግስታዊ ሰራዊትን ለማቋቋም የተሰጡት ምክንያቶች ተጠብቀው የሰራዊቱ ግንባታ እንዲቀጥል ማድረግ።

- የሰራዊቱ ተቋማዊ አደረጃጀት፣ ስልጣና እና ትምህርት፣ ሰራዊቱ በራሱ ስልጣን ለመያዝ የሚታገል አለመሆኑን እንዲያረጋግጥ መጣር።
- ለምልመላ የሚሆንን መመሪያ፣ የስነስርአት እና የስነምግባር ደንቦችን ማርቀቅ እና በወታደራዊ ስልጠና ወቅት ሰለህገ-መንግስታዊ ሰራዊትነት ለሚሰጥ ትምህርት የማስተማሪያ እና የጥናት ጽሁፎች ማዘጋጀት።
- የሚሰጠው ትምህርት በሚገባ መጨበጡን መገምገም የሚቻልባቸውን ዘዴዎች መቀየስ።

**3-2-2-** ህዝብ ስለ ህገመንግስታዊ ሰራዊት ምንነት እንዲያውቅ፣ በሰው ሃይል እና በገንዘብ ሃይል ለመርዳት እንዲንቀሳቀስ ማድረግ፤

- በስነ ጽሁፍ፤ በሬድዮ፤ በድረ ገጸት እና በምስል በተቀረጹ የፕሮፓጋንዳ ስራዎች ሰራዊቱን ለህዝብ ማስተዋወቅ፣ ህዝብ እስከዛሬ በየፖለቲካ ድርጅቶቹ

---

[2] ለምሳሌ፤ ኢ.ህ.አ.ግ እንደሚያምነው፤ ወያኔ በደሉን የሚፈጽመው የወታደራዊ ሀይል የበላይነት ስላለው በመሆኑ፤ ይህ ጥፋት እንዳይደገም ለማድረግ ሲባል፤ የኢ.ህ.አ.ግ ጦር ህገ-መንግስትን አስከባሪ ሁኖ መደራጀት ይገባዋል።

ስር ተደራጅተው በነበሩ የትጥቅ ትግሎች እና በህገ-መንግስታዊ ሰራዊቱ መካከል ያለውን ልዩነት በግልጽ እንዲያውቅ ማድረግ፤

- ትግሉ ከፍተኛ ብቃት እና እምነት ያላቸውን በርካታ ዜጎች እንዲያቅፍ ማድረግ፣ ለምሁራን በቂ ትኩረት ሰጥቶ መንቀሳቀስ፤
- ህዝብ የተለያዩ የትጥቅ ትግልን የሚያኪያሂዱ ሃይሎች አንድ ቢሆኑ የሚመጣውን ጠቀሜታ እንዲረዳ በማድረግ፤ አንድነትን ለመፍጠር ሰፊ ግፊት ማድረግ።

**3-2-3-** የፖለቲካ ድርጅቶች ለህገ-መንግስታዊው ሰራዊት ድጋፍ እና ትብብር እንዲያደርጉ ማድረግ።

- የጠመንጃ ትግል የጀመሩ የፖለቲካ ድርጅቶች የወታደራዊ ክንፋቸውን ከፖለቲካ ፓርቲ በመለየት ሰራዊቶቻቸው ከህገ-መንግስታዊ ሰራዊት ጋር እንዲያዋህዱ ጥረት ማድረግ፤
- ለሰራዊቱ ማሰተማሪያ የሚሆኑትን የትምህርት ጽሁፎች በጋራ ስምምነት ማዘጋጀት። ለህገ-መንግስቱ ሰራዊት ግንባታ ሃይላቸውን ያዋሃዱ ሃይሎች እና የትጥቅ ትግሉን ለማገዝ የሚፈልግሉ የፖለቲካ ድርጅቶች እንዲያጸድቁት ማድረግ። ከእዚህም ውጭ የሚገናኙ የፖለቲካ ድርጅቶች እና አጠቃላዩ ህዝብ እነዚህን የማስተማሪያ እና የጥናት ጽሁፎች በቀላሉ ማየት ወይም ማግኘት የሚችሉበትን ሁኔታ መፍጠር፤
- ሰራዊቱን የሚያስተምሩት ግለሰቦች በግልጽ የአስተማሪነት መስፈርት ተለክተው፣ በሁሉም የፖለቲካ ድርጅቶች ተቀባይነትን የሚያገኙበትን ሁኔታ መፍጠር፤
- ሰራዊት የሌላቸው የፖለቲካ ድርጅቶች በህገ-መንግስታዊ ጦር ምስረታ እና ተግባር እስከተስማሙ ድረስ፤ በፖለቲካ ክንፉ ውስጥ የሚወከሉበትን ሁኔታ መፍጠር፣ በሰራዊቱ ግንባታም ላይ ብቁ ተሳትፎ እንዲኖራቸው ማድረግ፤
- ሰላማዊ እና ህጋዊ የሆኑ ድርጅቶች ለህገ-መንግስታዊ ሠራዊት አዎንታዊ አመለካከት እንዲኖራቸው ለማድረግ፤ ጥብቅ ግንኙነት እና መመካከር የሚቻልበትን ሁኔታ ማመቻቸት፤
- የፖለቲካ ድርጅቶች፤ የትጥቅ ትግሉን ሁሉንም በእኩልነት ለሚያገለግለው ለህገ-መንግስታዊ ዴሞክራሲ ለሚታገለው ሰራዊት በመተው፤ በወያኔ ላይ ለሚያደርጉት ትግል ሰፊ የፖለቲካ ግንባር መስርተው እንዲንቀሳቀሱ መታገል፤
- ለመሳሪያ ትግል በተደራጁ ሃይሎች መሃከል የሚደረግ ግንባር የሰላምና የዴሞክራሲ ዋስትና ሊኖረው እንደማይችል በማስረዳት፤ በመተማመን ላይ የተመሰረተ ውህድ ሰራዊት ግንባታ ላይ እንዲያተኩሩ መጣር።

**3-2-4-** ግልጽ የሆነ የፖለቲካ አላማ ሳይኖራቸው በጸረ-ወያኔነት የሚንቀሳቀሱ የትጥቅ እንቅስቃሴዎችን በሚመለከት፤

- በአንድ ወጡ ህገ-መንግስታዊ ሰራዊትነት ዙሪያ የሚደራጁበትን ሁኔታ በአስቸኳይ መፍጠር።

3-2-5 ስለህገ-መንግስታዊ ስርአት ምስረታ እና ነጻ ተቋማት አመሰራረት ጥናታዊ ጽሁፎችን እያዘጋጁ ማቅረብ፤ ለህዝብ እና ወያኔን እያገለገሉ ለሚገኙ ተቋማት አባላት፤ በተለይ ደግሞ ለጦር ሀይሉ አባላት ማስተዋወቅ።

- ስለ ህገ-መንግስታዊ ጦር ጠቀሜታ እና ሀገራዊ ራእይ በተለይ በወያኔ ጦር ሀይል አባላት አካባቢ ሰፊ የማስተዋወቅ ስራዎችን መስራት፤

- በህገ-መንግስታዊው ጦር እና በወያኔ ጦር ሀይል አባላት መሀል በእርቅ መንግስት ምስረታ ዙሪያ ተቀራርቦ መስራት የሚቻልባቸውን መንገዶች ማፈላለግ፤ መፍጠር እና እንደ ድልድይ ሁኖ ማገልገል፤
- ወያኔን በማገልገል ላይ እሚገኙ ተቋማት ውስጥ የሚሰሩ ህዝባዊነት የሚሰማቸው አካላት፤ የኢህአግን ራእይ ለማሳካት በሚጠቅሙበት መስመሮች ማሰማራት፤ መንገዶቹን ማጥናት፤ ማፈላለግ እና መፍጠር።

## ማጠቃለያ

የኢትዮጵያ ህዝብ አርበኞች ግንባር ጠመንጃ የሚያነሳው ወድዶ እንዳልሆነ ቀደም ብለን ገልጸናል። ሰላማዊ የፖለቲካ ትግል ሀገራዊ እና ህዝባዊ ጠቀሜታ እንዳለው እንረዳለን። ጠመንጃን ስናነሳም በከባድ ሃዘን ነው። ጠመንጃን የሚያመልክ፣ ለሰው ልጆች ህይወት መጥፋት፣ ለመፈናቀል እና ለውድመት ደንታ የሌው አፍራሽ ባህላችን ያስከተለብንን የታሪክ ነቀርሳ እንድንገነዘበው ያደረገ የታሪክ ግምገማ እንዳለ፣ ግምገማውም ትክክል እንደሆነ እንገነዘባለን። የጠመንጃ ባህል ቀርቶ ልዩነቶቻችንን በሰላም እያስወገድን ተቻችለን እንድንኖር የምንችልበት ሁኔታ እንዲፈጠርም ታላቁ ምኞታችን ነው።

ይህም ተብሎ ግን፣ ወያኔዎችን የመሰለ ሰብአዊ ህሊና የሌላቸው የሰው አውሬዎች በነገሱበት፣ በህገ አራዊት በሚተዳደር ሃገር ውስጥ፣ ከላቀ የሞራል የባህል እና የስልጣኔ እድገት የሚነሳን የሰላማዊ የፖለቲካ የትግል ስልት በተግባር ማዋል ይቻላል የሚል እምነት የለንም። በወያኔም መጠን ያጣ ግፍ አሳሩን እያየ ተገፍቶ፣ በመኖር እና ባለመኖር የምርጫ ገደል ላይ እንዲቆም የተደረገው ህዝብ ከኢህአግ የተለየ የትግል አቅጣጫ የሚታየው አይመስለንም።

ህዝብ በግል እና በቡድን እየሸፈተ ነው። እንዲህ አይነቱ እውነታ በሰፈነበት ሃገር ውስጥ የፖለቲካ ድርጅቶች ‹እኛ ሰላማዊ የፖለቲካ ትግል አቀንቃኞች ስለሆንን ስለጠመንጃ ትግል አያገባንም› ሊሉ አይችሉም። አመጽ እንደሰደድ እሳት በሚቀጣጠልበት ሃገር ውስጥ፣ በሰላማዊ የፖለቲካ ትግል የሚያምኑ አካላትም ቢሆኑ ‹ጆሮ ዳባ ልበስ!› ብለው ሊቀመጡ አይችሉም። ከዚያ ይልቅ፣ የኢትዮጵያ ደህንነት ተቀዳሚ ጉዳያቸው እስከሆነ ድረስ፣ ሰላማዊው ትግል ተደናብሮ በሚገኝበት በዚህ ወቅት፣ ከአማጺያኑ መሀል ለእነርሱ አቋም የሚቀርቡትን ለይተው ማወቅ እና መደገፍ ይኖርባቸዋል።

በተለያዩ ምክንያቶች በፖለቲካ ድርጅቶች ውስጥ ተካትተው የማይገኙ ሌሎች ምሁራንም ቢሆኑ፣ ተመሳሳይ ሀገራዊ እና የሞራል ግዴታ አለባቸው። እኒህ ምሁራን፣ በእንቅስቃሴው ውስጥ በቀጥታ ተሳታፊዎች ሊሆኑ ባይችሉም፣ በእንቅስቃሴው አቅጣጫ እና አካሄድ ላይ ንቁ የሆነ ተጽእኖ ሊያሳድሩ ይገባቸዋል። ይህ ተጽእኖ በድጋፍ ኮሚቴዎች ዙሪያ ከመሰባሰብ ጀምሮ፣ በተለያዩ ሌሎች መንገዶች ሁሉ ሊገለጽ የሚችል ነው። ለምሳሌ፣ በስነ ጽሁፍ፣ በትንተና፣ በስትራቴጂ ጥናቶች፣ ስለ ግንባሩ አካሄድ ገንቢ የሆነ ሂሳዊ ተማግቦን በማቅረብ ወዘተ... ሊገለጽ ይችላል።

የአርበኞች ግንባር በሃገራችን በመርህ ላይ የቆመ የእርቅ መንግስትን መመስረት ለሀገራችን ችግሮች ዘለቄታዊ መፍትሄ እንደሚሆን ያምናል። ይህ ዘላቂ መፍትሄም ጽናት ባለው ተቋማዊ መሰረት ላይ እንዲቆም በማሰብ፣ ለሚመሰረተው ህገመንግስታዊ ስራዊት የጀርባ አጥንት ሁኖ ለማገልገል ቃል ገብቷል። የኢ.ህ.አ.ግ አደረጃጀትም፣ ይህንን የእርቅ መንግስት ምስረታን ዋነኛ አላማው አድርጎ የተነሳውን ራእይ ከጽንሱ ጀምሮ ለማስተናገድ የሚያስችል ሁኖ ስለሚሰናዳ፣ ማናቸውም ሀገር ወዳድ ዜጋ ሁሉ አስተዋጽኦውን ሊያበረክት የሚችልበት ስፍራ ይኖረዋል።

የኢ.ህ.አ.ግ ራእይ በአሁኑ ወቅት የወያኔን መንግስት ተቃውመው የቆሙ ወገኖችን ብቻ ሳይሆን፣ የወያኔን ሰራዊት ራሱንም ነጻ የሚያወጣ ነው። ይህ ራእይ የሃገራችን

የጦር ሃይል የአንድ ፓርቲ አገልጋይ በመሆን ከደረሰበት ተከታታይ ውርደት እና ጥቃት እራሱን ለመጀመሪያ ግዜ ነጻ ማድረግ የሚችልበትን፣ ፓርቲዎች በወጡና በወረዱ፤ መንግስት በተቀየረ ቁጥር እንደ ቤት ሰራተኛ የማይባረር፣ መሆኑን ለማረጋገጥ የሚሰራ ነው። ለሰራዊቱ፤ የሃገር እና የህዝብ ከለላ እና ጌጥ በመሆን በየግዜው የሚከፍለውን መስዋእትነቱን የሚመጥን ክብር የሚያላብሰውም ነው።

ስለዚህ፤ በአሁኑ ወቅት የወያኔን መንግስት እያገለገለ የሚገኘው ጦር በእርቅ መንግስት መመስረት በማመን፤ ኢህአግ ለተነሳለት የህገ-መንግስት ጦር ምስረታ እንዲነሳሳ ጥሪያችንን እናቀርብለታለን። ይህ ጦር የሚገባውን የሀገር ጠባቂነት ክብር ሊጎናጸፍ የሚችለውም፤ ሰላማዊ ዜጎችን ለአንድ ፓርቲ በመወገን በጠራራ ጸሀይ መንገድ ላይ በመጨፍጨፍ ሳይሆን፤ በራሱ በወያኔ ህገ-መንግስት ውስጥ ለይስሙላ ሰፍሮ የሚገኘውን የህገ-መንግስት አስከባሪነትን ተግባር ሲወስድ ብቻ ነው። ሀገራችን ውስጥ ተከስቶ ከሚገኘው ሁኔታ አንጻር ደግሞ፤ ይህ ሊሆን የሚችለው በመርህ ላይ የቆመ የእርቅ መንግስት በአስቸኳይ ሲመሰረት ብቻ ነው።

የአርበኞች ግንባር ወያኔን አስገድዶ ወደ ሰላማዊ የፖለቲካ መስክ መመለስ፣ ካልሆነም ማስወገድን የሚያስችለው ቀልጣፋው መንገድ የእርቅ መንግስት ምስረታ ጥያቄን በተጥቅ ትግል አማካይነት መግፋት እንደሆነ ያምናል ። የህዝባችንን አሳር እና መከራ አሳጥረን፤ ግንቦት ፈንጥቆት የነበረውን ጮራ በወያኔ አፈና እንዳይጨልም ማድረግ የምንችለው፤ ይህንን የግንቦት ተስፋ ሁሉም ህዝብ እና የፖለቲካ ድርጅቶች እንዲቋደሱት ለማድረግ ቆርጦ በአዲስ መልክ እራሱን ለማደራጀት የተነሳውን የኢትዮጵያ ህዝብ የአርበኞች ግንባርን በመደገፍ ስለሆነ፤ ማንኛውም የሀገሩን በጎ የሚመኝ ዜጋ ሁሉ ለዚህ የተቀደሰ አላማ ድጋፉን እንዲሰጠን እንጠይቃለን።